የክርስቲያን ኤድና የልማት አጋሮች ቅንጅት

ችሎታ ሲታወቅ

የወጣቶች አንድነት ሳምንት

ከሚያዚያ 26 - ግንቦት 2,1990 ዓ.ም.
አዲስ አበባ



ወጣቶች በችሎታችሁ ተማመኑ !

Christian Aid
May 1998

በብሩክ ማሞ
ደረጃ - አንደኛ

የክርስቲያን ኤድና የልማት አጋሮች ቅንጅት ችሎታ ሲታወቅ

የወጣቶች አንድነት ሳምንት

ከሚያዝያ 26 - ግንቦት 2,199 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

"ወጣቶች በችሎታችሁ ተማመኑ!" በሚል ርዕስ በተዘጋጀው
የአጭር ልብ ወለድ፣ ግጥሞችና የስዕል ሥራዎች ውድድር ላይ
ከ1ኛ እስከ 10ኛ የወጡ የኪነጥበብ ሥኞዎች ስብስብ

CCRDA

አዘጋጅ - ክርስቲያን ኤድ ኢትዮጵያ
☎ 61 58 12
✉ 20172 ኮድ 1000

አጠናቃሪ አያልነህ ሙላቱ
ታህሣሥ 1992
አዲስ አበባ

ማውጫ

አርዕስት	ገጽ
መግቢያ - በአያልነህ ሙላቱ	1
ወጣቱ የእድገት ምንጭ - በገዛህኝ ኡርጋ / የፖስተር ስዕል/	3
ፍለጋ - በመሰንበት ኃይሉ / አጭር ልብ ወለድ/	4
ይብራ ይቀጣጠል - በዘሪሁን ወርቅነህ / ግጥም/	6
አጉል ልማድ - በሮማ ታደሰ / የፖስተር ስዕል/	7
የወጣቱ ችግርና ተስፍው - በዩናስ አስናቀ / አጭር ልብ ወለድ/	8
ፍካት - በማንደፍሮ ንጉሴ / ግጥም/	10
የወጣቱ እምቅ ችሎታ - በሰናይት ወርቁ / የፖስተር ስዕል/	11
ተወርዋሪ ኮኮቦች - በዳዊት ፀጋዬ / አጭር ልብ ወለድ/	12
ተነስ አንተ ወጣት - በምህረት ተስፍዬ / ግጥም/	14
ለአገር እድገት - በአዳነ ኃ/ይለማሪያም / የፖስተር ስዕል/	16
ሰባተኛው ደብዳቤ - በነዋይ አፍርደው / አጭር ልብ ወለድ/	17
ወጣት የነብር ጣት - በአሸናፊ አለሙ / ግጥም/	19
ግብርና - በፍቱን ወርቁ / የፖስተር ስዕል/	21
ብሩህ ተስፍ - በተሾመ ደስታ / አጭር ልብ ወለድ/	22
አኩሪ ገድል - በዩናስ ወልደየስ / ግጥም/	24
ከልመና ውጣ - በዳዊት አስፍው / የፖስተር ስዕል/	25
እድለኛ ትውልዶች - በዮሴፍ ሽዋንዳኝ / አጭር ልብ ወለድ/	26
ሕይወት! ኑሮ ! ለወጣቶች - በእየሩሳሌም ብርሃኑ / ግጥም/	28
እስኪ ነጋ - በኢሳያስ ከበደ / የፖስተር ስዕል/	29
ወጣትነት በራሱ - በአላዛር በቀለ / አጭር ልብ ወለድ/	30
ትኩረት ለወጣቱ - በታየልኝ ጌታነህ / ግጥም/	31
ወጣቱና ችሎታው - በዘላለም ተረፈ / የፖስተር ስዕል/	32
መቅረዝ - በቀለሚ ወርቁ / አጭር ልብ ወለድ/	33
ዳግማዊ ወጣት - በአክሊሉ ወርቁ / አጭር ልብ ወለድ/	34
ተስፍ በጥረት ሲታገዝ - በኃይለ ልዑል ብርሃኔ / የፖስተር ስዕል/	35
ልማትና የወጣቶች ሚና - በትሁን ጎሹ / አጭር ልብ ወለድ/	36
ለነገው ብሩ ቀን - በደዊት ንጉሱ / ግጥም/	38
የወጣቱ ብሩህ ተስፋ - በሰለሞን መላኩ / የፖስተር ስዕል/	39
የወጣቶች እምቅ ችሎታ - በፍፁም ኃይሉ / አጭር ልብ ወለድ/	40
ወጣቱ - በተስፈኛው / ግጥም/	42
የወጣቶች አንድነት - በወርቅነህ በዙ / የፖስተር ስዕል/	43
የዳኝነት ሥራ	44

CCRDA

መግቢያ

የዘለዓለማዊነት መንፈስ፣ ያልሞተ ባይነት ስሜት፣ በልቡ ውስጥ በፀደቀው በወጣቱ የወደፊት ብሩህ ሕይወትና መልካም እንቅስቃሴ ላይ ተመስርቶ ጉልህም ይሁን ጥቃቅን ድጋፍ ማድረግ በአንድ አገር የእድገት ግንባታ ሕንፃ ላይ አንድ ጡብ እንደመጨመር ይቆጠራል። ወጣት ማለት እናት አገሩን ከአባቶቹ ከሁለንተናዊ መልኳ ጋር የሚረከብ ነው። ከአበው የተረከባትን አገር እሱም መልሶ የራሱን ጣእም ጨምሮ ለተተኪው ትውልድ አስረካቢ ነው። በአጭሩ ወጣት ስንል ዛሬ ሰው በሆነና ነገ ሰው በሚሆን ትውልድ መካከል ያለ አዲሱን በፍቅር ተቀባይ አሮጌውን በክብር ሸኝ ነው።

ይህ የዘመን ብቻ ሳይሆን የትውልድ ጭምር ተረካቢ የሆነ ወጣት፣ የሚረከበው ነገር ብቻ ሳይሆን የሚያስረክበው ኃይልም ይፈልጋል። ወጣቱ ትውልድ ዛሬ ትኩረት የሚሰጠው ኃይል ይጠይቃል። ከጐኑም ቆሞ "አይዞህ!" የሚለው ወገን ይሻል። ለፈጠራው..... ለእድገቱ ፈር የሚያወጣለት፣ ጭላንጭል ቀዳዳ የሚያሳየው ድርጅት ይፈልጋል። በዚህ ወቅት ነው ለኢትዮጵያ ወጣቶች አንድ የምሥራች የተሰማው። የወጣቶችን ችሎታ ለማውጣትና እውን ለማድረግ ክርስቲያን ኤድና ተባባሪዎቹ በሕብረት የወጣቶችን የፈጠራ ስሜት ያካተተ ፕሮግራም ነድፈው ብቅ አሉ።

የክርስቲያን ኤድ የእርዳታ ድርጅት የተመሠረተው በእንግሊዝ አገር ነው። የሚወክለውም የእንግሊዝንና የአየርላንድን አብያተ ክርስቲያናትን ነው። በአሁኑም ጊዜ ከ60 በላይ በሆኑ ደሃ አገሮች ተሰማርቶ የአስቸኳይ እርዳታ ክንዱን በመዘርጋት ላይ ይገኛል። የክርስቲያን ኤድ የገንዘብ ምንጮች አብዛኛዎቹ የእንግሊዝ አገር በጎ አድራጊዎች ናቸው። የእንግሊዝ መንግሥትና የአውሮፖ ሕብረትም ለክርስቲያን ኤድ ድጋፍ ይሰጣሉ። የክርስቲያን ኤድ ቅድሚያ የዘመቻ ትኩረቱ የድህነት ሁሉ ምንጭ በሆነው በማይምነት ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በአፈርና ውሃ አጠቃቀም፣ በጤና አጠባበቅና በአልሚ ምግብ አቅርቦት ላይም አስፈላጊውን ሥልጠና ይሰጣል። ክርስቲያን ኤድ በኢትዮጵያ እንቅስቃሴ የጀመረው ከ1962 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። ዘመኑም በአገሪቱ ላይ የረሃብ ደመና በሰፊው ያንጃበበበት ወቅት ነበር። የክርስቲያን ኤድ ፕሮግራም ያቀፈው በገጠርና በከተማ የሚኖረውን ችግረኛ ሕዝብ ነው። የእርዳታ ፕሮግራሙ ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በድህነት ሰንሰለት የታሰረውን ሕዝብ በምግብ እራሱን ለማስቻል፣ በገጠርና በከተማ መሠረተ ልማት ለመዘርጋት፣ ለሕፃናትና ለወጣቱ ትውልድ ልዩ እንክብካቤ ለማድረግና ትኩረት ለመስጠት ነው። እነዚህን ሥራዎች ተግባራዊ ለማድረግ ክርስቲያን ኤድ በአሁኑም ጊዜ ከ14 በላይ ከሆኑ አገር በቀልና ከአራት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የጋራ መድረክ ፈጥሮ ይሰራል። አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያን ኤድ የሚሰራው አገር በቀል ከሆኑና በአገር ውስጥ ከሚገኙ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ነው።

ክርስቲያን ኤድ ከአጋሮቹ ጋር በመተባበር ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ለወጣቱ ትውልድ ጠቃሚ የሆነ አንድ ፕሮግራም ዘርግቶ ነበር። ፕሮግራሙ የተካሄደው ከሚያዝያ 26 - ግንቦት 2 ቀን 1990 ዓ.ም. ነው። በዚህ በኢትዮጵያ ወጣቶች እንቅስቃሴ ላይ ባተኮረ አንድ ሳምንት በዓል ላይ የክርስቲያን ኤድና አጋሮቹ "ችሎታን እውን ማድረግ" በሚል መርህ ሥር የወጣቱን ክፍል በልዩ ልዩ ዝግጅቶችና ፕሮግራሞች ላይ በማሳተፍ ከፍተኛ ውጤት ያለው ተግባር አከናውነዋል። ስምፖዚየም ተደርጓል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባዛር ተከፍቷል። የመገናኛ ብዙሃን ሚና በሚል ርእስ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ታይቷል። የአጭር ልብወለድ፣ የሥነ-ግጥምና የፖስተር ስዕል ውድድሮች በወጣቶች መካከል ተካሂደዋል። ውድድሩ፣ የአገሪቷ ወጣቶች ወደፊት እንዳይራመዱ ከፊታቸው የተጋረጠውን ችግራቸውን እንዲያውቁ፣ በአንፃሩም ከፊት ለፊታቸው የተደቀነውን ጊዜያዊ አሜከላ ተደራጅተው በመጣል፣ ከአጥሩ ጀርባ ያለውን ብሩህ ተስፋ እንዲመለከቱ፣ ከዚያም የራሳቸውን አዲስ ሕይወት እንዲገነቡ፣ አዲስ የፀደይ ወራት እንዲያጠቡ አመቺ የመወያያ መድረክ ፈጥሮላቸዋል።

CCRDA

በወጣቶች አንድነት ሳምንት ላይ የተደረገው የሥነ ጽሑፍና የግጥም ውድድር አቢይ ዓላማ፣ የነገ አገር ተረካቢና መሪ ለሆነው ትውልድ የሞራል ድጋፍ ለመስጠት፣ የወጣቶችን ችግር ለመቅረፍ፣ ሕልማቸውንና ተስፋቸውን ተጨባጭ ለማድረግ ለወጣቱ ማህበራት ወይም ቡድኖች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ድርጅቶች ድጋፍ ለመስጠትና ለማበረታታት ነው፡፡ የወጣቱን እምቅ ችሎታ ማውጣትና በብሔብሄራዊ ልማት የወጣቱ ድርሻ ምን መሆን እንዳለበት መጠቆም፣ የእለት ተእለት ሕይወቱን መዳሰስ፣ አስተዋይነቱን ማስገንዘብና የፈጠራ ችሎታውን ማዳበር የኪነጥበብ ውድድሩ ሌላው ዓላማው ነው፡፡ በዚህ ውድድር ላይ 101 ግጥሞች፣ 83 አጫጭር ልብ ወለዶችና 110 የፖስተር ስዕሎች ቀርበዋል፡፡ ከየሙያ ዘርፋቸው የተመረጡ ዳኞች ተሰይመው በሁሉም መስክ 1-3 የወጡ ሥራዎችን መርጠዋል፡፡

የዚህ ስብስብ ሥራ እንቅስቃሴ የተጀመረው ከውድድሩ ውጤት በኋላ ነው፡፡ በየሙያ ዘርፉ ከ1-3 የወጡትንና የማሸነፍ እድል ያላገኙትን ሌሎችን ለውድድር የቀረቡ ሥራዎችን መርጦ በአንድ ቅጽ አሰባስቦ ለአንባቢያን የሚደርሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት በእጅጉ አስፈላጊ ነበር፡፡ ስብስቡ ለሁለት አበይት ቁም ነገሮች ይጠቅማል፡፡

አንደኛው በተለያዩ ጊዜያት ለውድድር እየቀረቡ የትም ወድቀው የቀሩ የጥበብ ሥራዎች እጣ ፈንታ ወደፊት ምን መሆን እንደሚገባው ያስተምራል፡፡ ሁለተኛው ስብስቡ እራሱ ለአገራችን የኪነጥበብ እድገት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ይህ ስብስብ ያተኮረው ዳኞቹ መርጠው ደረጃ በሰጧቸው ከ1-10 በወጡ ሥራዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ የፖስተር ስዕሎችን በተመለከተ ግን ከ4-10 ደረጃ የወጣላቸው ሥራዎች ስላልተገኘ ከ1-3ኛ የወጡትን ከወሰድን በኋላ የተለየ አሰራር ተከትለን ከ4-10 ያሉትን እራሳችን እንድንመርጥ ተገደናል፡፡

በሥነ ግጥምና በአጭር ልብ ወለዶች ላይ መጠነኛ የአርትኦት ሥራ ተካሂዷል፡፡ በተቻለ መጠን ግን ጎልተው የወጡ ስህተቶችን ከማረም ውጭ ብዙ ላለመንካት ጥረትም ተደርጓል፡፡

ዛሬ ወጣቱ ትውልድ "የምንረከበውን" እና መልሰን "የምናስረክበውን" ስጡን እያለ፣ የእያንዳንዳችንን በር አንኳኩቶ እየጠየቀን ነው፡፡ ቢቻል መልስ ከእኛ ስለሚጠብቅ፣ አሊያም ጥያቄውን እራሱ ጠይቆ እራሱ እንዲመልስ ይህን የመሰለ መፈናፈኛ መድረክ ልንከፍትለት በእጅጉ ተገቢ ነው፡፡

በእነዚህ በታተሙትና በሌሎችም ለሕትመት ባልበቁት፣ ለውድድር በቀረቡት የጥበብ ሥራዎች ላይ ወጣቶቹ ብዙ ነገር ተናግረዋል፡፡ ወጣትነት "ሕልም ነው"፣ "ንፋስ ነው"፣ "ሲያልፍ አይታወቅም" ብለዋል፡፡ ጤነኛም፣ በሽተኛም፣ ሐብታምም፣ ድሃ፣ ጨዋ፣ ባለጌ ለመሆን የሚቻለው በወጣትነት ዘመን መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡ ለውድድር ከቀረቡት ሥራዎች የአብዛኛዎቹ መደምደሚያ ግን "የወጣትነት ፍቅር፣ ንፁህና ነጭ ወረቀት ነው፡፡ ይህ ንፁህ ጨርቅ ግን በራሳችን በወጣቶች መቆሸሸ የለበትም" የሚል ነው፡፡ ትክክለኛ አቋም ነው፡፡ ትልቆች እናልማለን፣ ወጣቶች ግን ራእይ ያያሉና ይህ ራእያቸው ተጨባጭ እንዲሆን ቢቻል ከጀርባቸው ሆነን እንደግፋቸው ካሊያም ለራዕያቸው እንቅፋት አንሁንባቸው፡፡ የክርስቲያን ኤይድና አጋሮቹ እንደአበረከቱት አስተዋጽኦ፣ እኛም ለወጣቱ ትውልድ ጥንካሬ የሚያግዙ አመቺ ሁኔታዎችን እንፍጠርላቸው፡፡ የወጣቱም ትውልድ ከፍተኛው ክብር የመንፈስ ጥንካሬው ነው፡፡

አያልነህ ሙላቱ

CCRDA

ወጣቱ የእድገት ምንጭ



CRDA

በገዛኸኝ ኑርጋ
ደረጃ ሁለተኛ

ፍለጋ

መሰንበት ኃይሉ
ደረጃ አንደኛ

“በደህና እደሩ!“ እያለች ወደ ምዕራብ የምትንሸራተተዋ ፀሐይ ሰማዩን ፍም እያስመሰለች ወደ ማደሪያዋ ታዘግማለች፡፡ በስሱ የሚነፍሰው ነፋስ፣ ዕፅዋትን በለሰለሰ ስልት ያወዛውዛቸዋል፡፡ አዕዋፍ የሊመሽ ነው መዝሙራቸውን እየዘመሩ ወደ ጎጆዋቸው ይጣደፋሉ፡፡ ብቻ በአይነ ልቦናው ላየው ሁሉም ውበት ነው፡፡

“ሁሉንም ነገር ይህቺን ምድር ከረገጥንበት ጊዜ አንስቶ እናየዋለን፣ እንየው እንጂ አንመለከተውም“ ያሉትን አንድ አስተማሪዬን አስታወስኳቸው፡፡ እውነታቸውን ነው፣ ይህ ሁሉ ውበት ዛሬ አልተፈጠረም፡፡ ቀድሞም ነበር.... ግን የተመለከትኩት ዛሬ ነው፡፡ እጅ ለእጅ የተያያዙ ተራሮች፣ ለምለም መስክ፣ ከላይ ወደ ታች እየተወረወረ የሚፏልል ፏፏቴ.....አዎ! ሁሉም ነገር መስህብ ነው.... የመንፈስ ምግብ....

ቢሆንም ወደ እዚች ሰፈረ ሰላም የመጣሁት ተፈጥሮን ለማድነቅ፣ መንፈሴን ለማደስ አይደለም፣ ፍለጋ እንጂ፡፡ የማንነት ፍለጋ.... ለብዙ ዘመን ያጣሁትን እኔነቴን ፍለጋ.... ይህቺ ጀምበር ሳትጠልቅ ራሴን ማግኘት አለብኝ፡፡ ግን እንዴት?

ክፍል ቆጥሬያለሁ፡፡ እስከ አስራ ሁለት... ከዚያ በኃላ የትምህርት ፋይል ተዘጋ፡፡ “ትምህርት የፋራ ነው.... ደብተር የኩሊ ነው“ የሚለውን መፈክር አንግቤ ከአራዳዎቹ ጎራ ተሰለፍኩ፡፡ እነርሱ የሚሆኑትን እሆናለሁ፣ እነርሱ የሚያደርጉትን አደርጋለሁ፡፡ “ጃሬ የነፋን” ዕለት የቪዲዮ እና የጠላ ቤቶች መቀመጫዎች በእኛ ጢም ይላሉ፡፡ በጫት ቀንበጦች ጉንጮቻችንን ወጥረን፣ በሲጋራ ጪስ እያማግን፣ በጠላ እያወራረድን “መጫጫስ” ነው፡፡ በቃ የራሳችንን ልዩ አለም ፈጥረን በምኞች ባህር ውስጥ መዋኘት፡፡ ማዕበል የማያስቸግርበት፣ አውሬዎች የማይተናኮሉበት ፀጥ እረጭ ያለ ባህር....

ያልተገኘ ዕለትም ግንቦችን እና ምሰሶዎችን ተደግፈን፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ወሬ ማውራት፡፡ ወጪ ወራጁን እያዩ መተረብ.... ማውካካት..... እንደዚሁ እንደሆንን ፀሀይ ወጥታ ትጠልቃለች፡፡ አሁን አሁን ሳስበው ግርም ይለኛል፡፡ ከእኛ ከሰዎቹ ግዑዞቹ ነገሮች በልጠው ሲገኙ.... እኛ እዚያ የምንገተረው ያለምንም ጥቅም ነው፡፡ እነሱ ግን እየሰሩ ናቸው፡፡ ግንቦቹ ለከለላነት፣ ምሰሶዎቹም ቢሆኑ የመብራት አሊያም የስልክ ገመዶችን በመሸከም ያገለግላሉ፡፡

ግን አሁን፣ ሁሉም ነገር ሰልችቶኛል፣ አንገሽግሾኛል፡፡ እስከ መቼ እንደዚህ ሆኜ እኖራለሁ? ስለዚህ ራሴን መፈለግ፣ ማንነቴን ማወቅ አለብኝ፡፡ ታዲያ! እኔነቴን የት ነው የማገኘው? ከጋኖች ስር፣ ከዙርባ ጫቶች መሃል? ወይስ.....፡፡ መልስ ያልተገኘለት ጥያቄ.....

ጨነቀኝ፡፡ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ወዲህ እና ወዲያ እንጎራደድ ጀመር፡፡ ድንገት የፀሐይ ድምፅ ከአድማስ ተራሮች ስር አስተጋባ፡፡

“በፍፁም፣ አንተነትህን በእነዚህ ነገሮች ውስጥ አታገኘውም”
“ታዲያ ከየት? ከየአስፋልቱ ጥጋጥግ?”
“ዳግም ወደ ስህተት ውስጥ አትግባ፡፡ መልሱ ከዚህ የተለየ ነው”

CCRDA

“መልሱ የተለየ ነው?”

“አዎን!” አለችኝ መልሳ፡፡ ድብቁን ማንነቴን የት እንደሚገኝ ለማወቅ ጓጓሁ፡፡

“እባክሽ ንገሪኝ እኔ የት ነው የምገኘው?”

“አንተነትህን ከደብተሮችና መፃህፍት ውስጥ ፈለገው፡፡ ማንነትህን ስራዎችህ መሐል በርብረው፡፡ ራስን መምሰል በዋዛ አይገኝምና! ትዕግስትን፣ ሳይታክቱ መስራትን፣ ላብን ይሻል፡፡ ጠንክረህ ስራ..... አንተነትህን ታገኘዋለህ” ይህንን ብላኝ ወደ ማደሪያዋ ገባች፡፡

“.....ራስህን በስራዎችህ መሀል ፈልገው፣ ታገኘዋለህ፡፡” ቃሏ በአዕምሮዬ ውስጥ አስተጋባ፡፡ እኔነቴን አገኘሁት፡፡ አሁን መሸቷል፣ ፀሐይ ጠልቃለች፡፡ ነገ ግን በምስራቅ ተራሮች በኩል አዲስ ጮራ ትፈነጥቃለች!፡፡ ብሩህ ቀን.....

CCRDA

“ይብራ ይቀጣጠል”

በዘሪሁን ወርቅነህ
ደረጃ አንደኛ

ጊዜ ቃሉን ላያጥፍ.....ተግባሩን ላይረሣ፣
ዛሬም ሌላ ቀንን.....ነግን ሊወልድልን፣
አርግዞ አምጦ.....ጓዙን ሲጭንልን፣
ማሙሽነት ቀርቶ.....ልጅነት ተረስቶ፣
በጊዜ ሹም ሽረት.....አፍላነት ሲተካ፣

እንቡጡ ዕድሜአችን.....ወርቃማው ጊዜአችን፣
ትኩሱ ኃይላችን.....ሞቃቱ ደማችን፣
ዳብሮና ጎልብቶ.....ፈርጣማው ክንዳችን፣

ከኢኮኖሚው ዋልታ.....ከግብርናው ተራ፣
ከኳስ ከአትሌቲክሱ.....ከእስፖርቱ ጋራ፣
ከምርምሩ ዘርፍ.....ከሳይንሱ ጎራ፣
ከስዕል ከሙዚቃው.....ከጥበቡ ሥፍራ፣

እንደ ተሰጥኦአችን.....ሰፍቶ አድማሳችን፣
በእውቀት ታንፆ.....ብሩህ አእምሮአችን፣
ለአልፋና አሜጋ.....ለአዲስ ግኝታችን፣
ለሐገር ብልፅግና.....ለልማት ፈርጃችን፣
አብቦ ስናየው.....ቡቃያው ተስፋችን፣

ነፍስ ሲዘራብን.....እምቅ ችሎታችን፣
መሠረቱን ሲጥል.....ለነገው ግባችን፣
ለወሳኙ ምዕራፍ.....ለበጎው ጥሪያችን፣
ተደራጅቶ መስራት.....ማምረት ነው ድርሻችን፣
የእኛ የወጣቶች.....ተምሳሌነታችን፡፡

የእድገት ማነቆን.....ወንጀልን አጥፍተን፣
ከጫት ከሲጋራ.....ከአልኮል እርቀን፣
ዝሙት ሴሰኝነት.....ደባል ሱሶች ፍቀን፣
ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ.....ከችግር ተላቀን፣
በአኩሪ ባሕላችን.....እንደ ፀሐይ ደምቀን፣
ማየት ነው ትልማችን.....የዛሬው ሚናችን፡፡

ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ..... ይሠማ ድምፃችን፣
ይብራ ይቀጣጠል.....ይለኮስ ሻማችን፡፡

CCRDA

አጉል ልማድ



በሮማ ታደሰ
ደረጃ ሦስተኛ

CCRDA

የወጣቱ ችግርና የወደፊት ተስፋው

በዮናስ አስናቀ
ደረጃ ሁለት

ሰፈውና ዘመናዊው ቢሮ በጣም ውብ ነው፡፡ ተስፋሁን ከምቹ ወንበሩ ወደፊት ሳብ ብሎ ተቀምጠ ጠረጴዛውን በክንዶቹ ተመርኩሟል፡፡ ከቀናት በፊት ተገኝቶበት በነበረው የወጣቶች ስብሰባ ላይ ተቀድቶ የነበረውን የተሳታፊዎች ንግግር ሲያዳምጥ ነው የቆየው፡፡ ስንት ጊዜ እንደሆነ ባያስታውስም፣ ደጋግሞ ያዳመጠው የአንድ ወጣት ንግግር ግን ከሌሎች ጋር ተደምሮ ልቡን ነክቶታል፡፡ አሁንም አጠነጠነና እሱኑ ደግሞ ማዳመጥ ጀመረ፡፡

"……ቤተሰብ ያቅሙን አሟልቶ ሲያስተምረን፣ ሰው ሆነን ራሳችንን የምናስተዳድርበትንና እነርሱንም የምንደግፍበትን ቀን እየናፈቀ ነበር፡፡ ያ! ግን ሳይሆን ቀረ፡፡ እኛ ባደግን ቁጥር ቤተሰቦቻችን ያረጃሉ፡፡ መጦር በነበረባቸው ወቅት እኛ አልደረስንላቸውም፡፡ ዛሬም ያባቶቻችንን የጡረታ ሳንቲም ጠብቀን የምናድር ብዙ ነን፡፡ ከካልሲ አቅም እንኳ አሁንም ከቤተሰብ ነው የምንጠብቀው፡፡

"……በዚያ ላይ ማህበረሰቡ በመልካም አይኑ አያየንም፣ ያበሻቅጠናል፡፡ በስመ ወጣት ሁላችንንም ከሌላ ጋር ያዛምደናል፡፡ ሌላው ቢቀር አውቶብስ ላይ እንኳ ነፃነት የለንም፡፡ መብታችን ተደፍሮ ብንናገር "ለመስረቅ ስላልተመቸው ተናዶ ነው" እንባላለን፡፡ ልብሳችን ስላደፈና ወጣት ስለሆንን ብቻ ኪሳቸውን እየፈተሹ ይጠቋቆሙብናል፡፡ መንገድ ጠፍቶን ብንጠይቅ በቅን መንፈስ የሚያስተናግደን የለም፡፡ አጭበርባሪ ተደርገን እንቆጠራለን፡፡ በገበያ መሃል ከታየን ሌቦች ነን፡፡ የፖሊስ ቆመጥ እንኳ የሚበረታው በእኛ ላይ ነው፡፡ ስለመብታችን ከማሳወቅና ጥፋታችንን ከማረጋገጡ በፊት ጭሜና እርግጫ ያወርዱብናል፡፡

"……ለቤተሰብ ሸክም መሆናችን ሀሊናችንን እየበጠበጠው፣ መንፈሳችንን የሚያድስ መዋያ እንኳ አጥተን ደጃፋችን ላይ በተቀመጥን ወጪ ወራጁ ያብጠለጥለናል፡፡ ገላምጠውን እያለፉ ተናጋሪ ያደርጉናል፡፡

"……እነኝህና ሌሎችም ከተስፋ ውጪ ሲያደርጉንና ጊዜው አልሄድ ሲለን ለጊዜው ከሀሊና ወቀሳና ብስጭት የተገላገልን መስሎን እንደሚጎዱን በምናውቃቸው ዕፆች ውስጥ በመደበቃችን፣ ለሀገር ሸክም የሆንን፣ ተስፋ ቢስ መሆናችንን ሊነግሩን ይጣደፋሉ፡፡ በመፀሐፍትና መገናኛ ብዙሀን ከማስተማር ይልቅ ተራ ዝለፋና ወቀሳ ይቀናቸዋል፡፡

"……ወጣቱ አፋ ምድጃ፣ ቀለቡ እንደ ፍየል ቅጠል፣ ባህሪው ሴታሴትና ልክስክስ፣ ቅንጣት ታህል የሀገር ፍቅር የሌለው….. ገለመሌ……" በማለት ከህብረተሰቡ እየራቅንና ጥላቻን እየቋጠርን እንድንሄድ ያደርጉናል፡፡ የተሻለ ህይወት እንድንኖር ምን የተደረገልን ነገር አለ? "ቁጭ ብለው ስራን እንደመና ከመንግሥት ይጠብቃሉ" ተባልን እንጂ የትኛው የሙያ ት/ቤት ገብተን እንድንማር እድሉ ተመቻቸልን? ኑሮ አልመች ሲለን፣ ሆዳችንን እየራበው ወጣትነት ሲናፍቀንና የምናየው ሁሉ ተስፋ አስቆራጭ ሲሆንብን — በጫትና በሲጋራ ውስጥ ተደብቀን ለጊዜውም ቢሆን ራሳችንን ለመርሳት ብንሞክር የሚያስደንቀው ምንድነው? መድሃኒት መስለውን እንደዋዛ የጀመርናቸው ዕፆችና የአልኮል መጠጦች ጭንቅላታችንን አደንዝዘውት ለሱስ ተገዢ፣ ለምንም ነገር ግድ የለሾች፣ በህይወታችን ተስፋ ቆርጠን እንዲሁ የምንመላለስ ፅድኖች ቢያደርጉን፣ የነገ ጥሩ ሀገር ተረካቢ ልንሆን ባንችል፣ የሚወቀሰው ማነው? የገቢ ምንጭ ሲያጥረን ሱስ የሆኑብንን ዕፆች ለማግኘት ስንል ምን እንዳናደርግ ነው የሚጠበቀው? ስለወጣቱ ስናነሳ ደርሰን ከመዝለፋችን በፊት ብዙ…. በጣም ብዙ አብረን ልናያቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ……"

ከዚህኛው በኋላ ትንሽ ቆይቶ በዕልህ የታፈነ የአንድ ወጣት የብሶት ንግግር ቀጠለ፡፡

CCRDA

“.....ወጣቱ እንዲህ ነው፣ እንዲህ ያደርጋል ማለቱና ማንቋሸሹ የሚበልጡንን እንድናከብር አያስገድደንም፣ ጨዋ እንድንሆንም አያደርገንም፡፡ ይልቁንም እስካሁን እንደተባለው ህብረተሰቡን እንድንጠላ፣ ለማንም ከበሬታ እንዳይኖረን፣ ለህግ እንዳንገዛና ከባህልና ከስርዓት እንድንወጣ ነው የሚገፋፋን.... ” ቴኘሪኮርደሩን ተጫነና አቆመው፡፡ ህሊናው ማሰላሰል ጀምሮ ነበር፡፡

“የወጣቱ ተስፋ ምንድነው?” አቃጨለበት.....
ይህ የሁሉም ጥያቄ ሊሆን ወቅቱ ግድ እንደሚል ተረድቷል፡፡ የነገሩ አሳሳቢነት ሰርስሮት ገብቷል፡፡ በፊት.....በየመንደሩ ሰውነታቸው ሞልቶ፣ ደረታቸው አብጦ፣ የሚያያቸውን ወጣቶች ሁሉ የደላቸው አድርጎ ያስብ ነበር፡፡ ለነገ ምንም ተስፋ ሳይኖራቸው..... ዛሬን ለመሸንገል ራሳቸውን የሚያታልሉ መሆናቸውን የተረዳው አሁን ነው፡፡

በርግጥ ወጣቱ “ሥራን ከመንግሥት ይጠብቅ” የሚል ዕምነት የለውም፡፡ በአንድ ወቅት ስለኢትዮጵያ ወጣቶች የፈጠራ ችሎታ ያነበበው አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ የወጣቱን ዕምቅ ችሎታ አስገንዝቦታል፡፡ ሁኔታዎች ቢመቻችላቸው የራሳቸውን ስራ ለመፍጠርና ለማዳበር ንቁ አዕምሮ እንዳላቸው ተረድቷል፡፡ በፖለቲካው መስክ፣ በስፖርቱና ብዙ ሀገሮች በልጠውን በማታዩባቸው ነገሮች ሁሉ ወጣቶቹ የበለጠ ችሎታ አላቸው፡፡ ይህን ሀይል ሀገሪቷ በአግባቡ እንድትጠቀምበት ለማድረግ ደግሞ ሀላፊነቱ ከባድ እንደሆነ ተሰማው፡፡

አገጩን ሁለት እጆቹ መዳፎች ላይ አስደግፎ ጠረጴዛው ላይ አፈጠጠና ማሰብ ጀመረ፡፡ ትንሽ ቆይቶም የተስፋ ጭላንጭሎች ብልጭ አሉበት፡፡ ፈጠን ብሎ በወረቀት ላይ አሰፈራቸው፡፡ ለወጣቱ የወደፊት ህይወት ብርሃን ናቸውና ሊታገልላቸው ቆረጠ፡፡

ወቅቱ የነፃ ገበያ ስርዓት የታወጀበት እንደመሆኑ፣ የግሉ ኢኮኖሚ ዘርፍ ወጣቱን ሊጠቅም በሚችልበት መስክ መዋዕለ ንዋዩን እንዲያፈስ ጥረት ቢደረግ፣ ስራ የማግኘት ዕድልን ያሰፋል፡፡

መንግስት የሚቀርፃቸው የልማት ፖሊሲዎች ሁሉ ከወጣቱ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘቡ እንዲሆኑ መጣር፡፡ ይኸውም ወጣቱን ማዕከል ያላደረገ ልማት እምብዛም ግቡን ስለማይመታ ወጣቱ ያለውን ዕምቅ ችሎታ ለመጠቀም ከራሱ ባሻገር ሀገሩንም የሚጠቅምበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡

የግልና የመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲስፋፉ መጣር፡፡ ይኸውም ወጣቱ እየሰራ በመማር እራሱን እንዲያሻሽልና ለወደፊት ህይወቱ ስኬታማነት በፅኑ መሰረት ላይ እንዲጥል ይረዳዋል፡፡

የፃፋቸውን ደጋግሞ አነበበና ለተግባራዊነታቸው ሳያሰልስ ሊታገል መሃላውን በፊርማ አረጋገጠ፡፡ በክልሉ የወጣቶች ጉዳይ ዘርፍ ሃላፊ እንደመሆኑ ከሱና ከባልደረቦቹ ከዚህም በላይ እንደሚጠበቅ አምኗል፡፡ ያሰበው ከተሳካ ደግሞ ወጣቱ ፍሬያማ ሆነ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ.....

የተሳካለትን ያህል ተፍነከነከ..... ደስ አለው፡፡

ወረቀቱን በጁ እንደያዘ የስራ ባልደረቦችን በማሳመን ትግሉን ሊጀምር ከቢሮው ሲወጣ በልቡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚመለከታቸው አካሎች ሁሉ ቀና ትብብር ለማድረግ እንዲነሱ እየፀለየ ነበር፡፡

CCRDA

ፍካት

በማንደፍሮ ንጉሤ
ደረጃ ሁለተኛ

ጨረቃዋ ደምቃ ፍንትው ብላ ወጥታ፣
ከተራራው አናት በግርማ ተኝታ፣
በወርቃማ ገጿ በሳቅ በፈገግታ፣
ሀዋ አድማሱን ሞልታ.....

አሻግራ አቆልቁላ ምድርን ስትቃኛት፣
በፍቅር በግርማ ወጣቱን አየሁት።።

ውበቷን ሲያስተውል ውበቷን ሲያሞግስ፣
ያለ ጽምዕ ያለቃል በአርሞሞ ሲላወስ።።

መስከረም አበባ ብርሃንን አርግዞ፣
የነሐሴ ግርዶሽ ደመና ደንግዞ።።

ጨለማው ሲፈካ በረሃው ሲለማ፣
ምድር ተጎናጽፋ አረንጓዴ ሸማ።።

ገበሬው ሲደሰት ወዛደር ሲጨፍር
ምሁር ሊቃውንቱ ፍሬ ቃል ሲያስተምር።።

ነጠላ ጥንድ ሆኖ ሀይሉን አጠንክሮ፣
ወጣት ህብር ፈጥሮ፣
እጅ ለእጅ ተቋጥሮ።።

ቀማኛ ዘራፊ ሴተኛ አዳሪነት፣
ክፋ ጉስቁልና የምንዱባን ሕይወት፣
ረሃብ እርዛት የሕፃናት ብሶት፣
ብርሃን ሲያበራ ህብረ ወጣትነት።።

ወጣት ሊቃውንቱ ፈላስፋ ደራሲው፣
ኬሚስት አንጥረኛው ፖይለት መርከበኛው፣
ወጣቱ ምሁራን ብርሃንሽ የገባው።።

ፍርጥም ሀይል ጉልበቱ፣
እምቁ እውቀቱ።።

ያለስስት ያለንፍገት ሲለግስሽ፣
ኢዛና እንቁ ታሪክሽ።።አክሱም ስልጣኔሽ ሲያብብ ሲያቆጠቁጥ፣ ሲፈካ ሲበራ የብርሃን ጮራ፣
እየሁ እውን ራዕይ ከምስራቅ ቀንድ ላይ፣ ከምስራቅ ተራራ።።

CCRDA

የወጣቱ እምቅ ችሎታ



በሰናይት ወርቁ

CCRDA

ተወርዋሪ ኮኮቦች

በዳዊት ፀጋዬ
ደረጃ ሶስተኛ

ወጣቶች በደማቸው የሚዘዋወረው የእውቀት ሾርባ ነው፡፡ በሕይወት አሳንሰር ላይ ወጥተው የአለምን እንቆቅልሽ ለመፍታት የለበሱት የጥበብ ማሊያ ምቹ ነው፡፡ አፍለኛ እድሜያቸው ለጭንቅላት ጅምላስቲክ ገና በጥዋቱ ይንቀሳቀሳል፡፡

አለምን ለመለወጥ የሚያስችል መሣሪያ በእጃቸው ይዘዋል፡፡ የሕይወት ሚስጥር እየበለቱ ለማውጣት በየልቦቻቸው አንገት ላይ የክብር ሜዳሊያ አንጠልጥለዋል፡፡ የሳይንስን ክራቫት አስረው የምድርን ፂም ይላጫሉ፡፡ እድሜያቸው ፎቶ እንዳለበት አልበም ነው፡፡ ሲከፈት ሕይወት ከሳች የሆነ ሥዕል የሚገኝበት.....

ወጣቶች ከሰፊሮስ የከበረ ድንጋይ ይበልጥ ያንፀባርቃሉ፡፡ መዓዛቸው ከናርዶስ ሽቶ የበለጠ ያውዳል፡፡

ወጣቶች አያሌ የሕይወት ቡጢ ቢያርፍባቸውም፣ ይህንን ሁሉ አሸክላ ተቋቁመው የሚጣፍጥ መረቅ ይሆናሉ፡፡ እምቅ ችሎታቸውን ለተገነዘበ በመፍትሄ ቀዳዳ ውስጥ የሚጠልቁ ከምሱሮች ናቸው፡፡ እድሜያቸውን ለተጠቀመበት ሸካራውን የሕይወት ገላ የሚያለሰልስ ቅባት ነው፡፡

የወጣቶች ጉልበት ለልማት የአልጋ ላይ አንሶላ ነው፡፡ የኢኮኖሚውን ፍርሃ ለማራመድ በአስተማማኝ ሁኔታ የተነጠፉ ሃዲዶች.....

አለምን የሳይንስ ፀበል እየረጫት ያሉት ወጣቶች ናቸው፡፡ ወጣቱን ትውልድ በደፈናው የጥፋት ምንጭ እንደሆነ አድርገን ከተመለከትን፣ ሕሊናችን ከእውነት ፍሬም ውስጥ አፈንግጧል ማለት ነው፡፡ ወጣትነት የጥፋት ኮሮጆ ብቻ ሳይሆን የእርባና መያዣም ኮዳ ነው፡፡

በትክክል ወጣትነት ወደሚቀጥለው የሕይወት ፌርማታ የሚያደርስ ምርጥ ሾፌር ነው፡፡ ወጣቶች በምድረበዳ ላይ እንደምትበቅል ዛፍ፣ በበረሃ ውስጥ እንደምትለመልም ሳሮን ዘወትር ይፈካሉ፣ ሠርክ ፍሬው እንደሚበላ በቆሎ ውስጥ እንደሚበቅል እንኮይ ይጓጓሉ፡፡

በውስጣቸው የሚንቀለቀለውን የፈጠራ ፍም ላስተዋለ ትኩስ የጥበብ ብስኩት መሆናቸውን ያያል፡፡ አለም ቀስ እያለች የምትበላ የሕይወት ማር.....

ወጣትነት ወንዝ እንደተተከለ ቁጠማ ነው፡፡ በሚፈሰው ውሃ ይበቅላል.... ያድጋል፡፡ ወጣቶች በስሜት ነበልባል እየነደዱ የሚከስሙ ብቻ አይደሉም፡፡ ራሳቸውን በጥበብ ጋራዥ ውስጥም ያንፃሉ፡፡ ወጣቶች ሀይልን የመጠጡ ክብሪቶች ናቸው፡፡ በተፈለጉ ጊዜ ሲለኮሱ የአገርን ቆሻሻ የሚያቃጥሉ ንፁህ እሳቶች....

CCRDA

በየልቦቻችን ታዛ ስር ስፍራ ካገኙ፣ ለትውልድ የሚተላለፍ የአገርና የሕዝብ ቅርሶችን የሚያነሱ ካሜራዎች መሆናቸውን እናውቃለን፡፡ በእርግጥ በአሁን ሰዓት የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወጣት የየዕለት ኑሮ ሲታይ፣ በከፍተኛ ፍጥነት ከሚነፍሰው የቴክኖሎጂ ነፋስ ጋር እኩል ነፍሶ ልብ ለልብ ሊዋሃድ አልቻለም.... ይህ ማለት ደግሞ የበቀሉበትን ዘር አለማወቅ ማለት ነው፡፡

ወጣትነት በአንድ ወቅት መንጠፍ እንደማይቀር ያልተገነዘብን ወጣቶች እድሜያችንን እየቀዳን የትም እያፈሰስነው ነውና! በማለዳ ነቅተን የሕይወት መቅረዛችንን እንለኩስ፡፡ አዎን! ተጨባጭ የሆነ ተስፋ ከእድሜያችን ግርጌ ስር አለ፡፡ ማንነታችንን ያሰርንበትን ሰንሰለት መበጣጠስ የምንችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ያጠለቅነውን ጭምብል አውልቀን ራስን በመሆን.....

በአጠቃላይ ወጣቶች..... የፍቅር ናሙና፣ ከወርቅ ጠልሰም የሚመረጥ ችሎታ፣ በጥበብ የናረ የእውቀት ሙዚየም እነዚህን ሁሉ ያቀፉ አስገራሚ ፒራሚዶች ናቸው፡፡ ከጭንቅላታቸው እየተነነ የሚወጣው የእውቀት ሽታ፣ ከባርሠነት ዛፍ የበለጠ አስደሳች መዓዛ አለው፡፡

የፈጠራን አክሊል በውስጣቸው የጻፉ፣ የብርሃን ውሽንፍር በልባቸው የሚያካፋ፣ ጨለማን የሚንዱ፣ የብርሃን ዘንጎች፣ የመፍትሔ ምሶሶ ናቸው፡፡

እናም! ወጣቶች ጥቅጥቅ ያሉ የእውቀት ጫካዎች ናቸውና! የእድገትም ሆነ የቴክኖሎጂ ድርቅ እንዳይመታቸው ግዙፍ የሞራል ኪስ እንሁናቸው፡፡ ያኔ! ከጥበብ የላቁ ጥበቦችን እዚሁ ካዝና ውስጥ እናገኛለን፡፡

CCRDA

ተነስ! አንተ ወጣት

በምህረት ተስፋዬ
ደረጃ ሶስተኛ

የሚያስብ አእምሮ እጆች የሚሠሩ.....
አድገው ተመንድገው ለፈጠራ ሲያድሩ፣
ሥራን ሲያሻሽሉ፣
አለምን አጣፍጠው የአለም ጨው ሲባሉ፣
ለዚህ ያልታደሙ.... ለዚህ ያልታደሉ.....
ታዩኝ ተዘርግተው ምፅዋት ሲለምኑ.....
በየኪወስኩ ቤት አልኮል ሲያንቃርሩ....
እድል ሲያማርሩ.....
ወለም..... ዘለም ሲሉ።።

የልመናን ባህል፣ የስርቆትን ጀብዱ፣ ለሰው ዘር ሲያበስሩ
ሌት ተቀን ሲዞሩ።።
ተመልከት አንተ ወጣት.... አንተ ድንግል ጉልበት፣
ቀና በል አስተውል የትውልዱን ንቅዘት፣
የትውልድን ንፍዘት..... የግመል ሽንት እድገት፣
ወደኋላ ማዝገም..... ወደኋላ ማየት..... ወደኋላ መቅረት፣
ለርሃብ ለእርዛት እጅን አስሮ መስጠት።።

ስንፍና ተብትቦህ፣ ተስፋ መቁረጥ ይዞህ፣
በከንቱ ሲያስረጅህ ..... በቁም ሲያጋጅህ.....
"ስራኮ አጥቼ ነው" በሚል አዲስ ፈሊጥ፣
ውስጥ ውስጡን አቃጥሎ....
አንድዶ ሲፈጅህ፣ ለሞት ሲያዘጋጅህ።።
ተነስ! አንተ ወጣት.... አንተ ድንግል ጉልበት፣
በርሃብ ንግስበት፣ በስራህ አሳየው፣ ዙፋንህን ዘርጋበት።።

ጃፖን አሜሪካ ኢታሊ ስዊድን፣
ፈረንሳይ እንግሊዝ ሩሲያን ጀርመን፣
አይደለም በምፅዋት..... መች ብቻ በፀሎት፣
አይደለም በተአምር... አይደለም በችሮት፣
ሌት ከቀን ግረው ነው ለዚህ የደረሱት።።

እናም አንተ ወጣት... ከጎዳናው ተነስ! ከተጋደምክበት...
እጅህን ለምፅዋት ከዘረጋህበት፣
ተነስ! ከጫት ቅሚያው..... "ዱአ" ከያዝክበት
እልፍ አእላፍ አማልዕክት ከምትጠራበት
ውጣ ከፖርቲው ቤት ከምትደንስበት...

CCRDA

ቅራቅንቦ ባህል እሽኮኮ ካልሀበት
ውጣ ከየጓዳው ከምትጦርበት
የተስፋ ጭላንጭል ከደበዘዘበት፡፡


ኮስማናው ፈላስፋ ዞሮ ታሪክ አውሪ.....
ከንቱ ጦም አዳሪ.....
ስደት አስተማሪ
የሌለው መዋያ..... የሌለው ማደሪያ.....

ሁላችሁ..... ሁላችን..... ተነሱ! እንነሳ!
የአምናው የካቻምናው የጥንቱ ይረሳ.....

እንሁን አዲስ ፍጥረት.... ቃል ኪዳን እንግባ.....
የአምራች ችቦ እናንሳ... እንቁም በጥምረት
አእምሯችን ይስላ.... ለአዲስ ግኝት.... እውቀት
ጉልበታችን ይዋል ..... ለአገር ልማት እድገት፡፡

CCRDA

ለአገር እድገት



በአዳነ ኃ/ማሪያም

CRDA

ሰባተኛው ደብዳቤ

በንዋይ አፋርደው
ደረጃ አራተኛ

በተደጋጋሚ በፈፀመው የተለያዩ ወንጀሎች አምስት ዓመት የተፈረደበት የ19 ዓመቱ ወጣት ከዘብጥያ ቤት ከሁለት ዓመት በኋላ ለጓደኞቹ የፃፈው ሰባተኛው ደብዳቤ፡፡

መጋቢት 20 1990

ይድረስ ለውድ ጓደኞቼ! ለመስፍን.... ለደበበ.... ለእስክንድርና ለአዝመራ..... ለጤናችሁ እንደምን ከረማችሁ? በሰባተኛው ደብዳቤዬ በቅጽል ሳይሆን በእውነተኛ ስማችሁ በመፃፌ ትንሽ ሳያደናግራችሁ አይቀርም፡፡ አትደናገጡ... ከጤነኝነት መንፈስ የመጣ ነውና! አትጠራጠሩም፡፡ የእኔም ሮሲ መባል ከዛሬ በኋላ ያቆማል፡፡ የእኔም ብቻ ሳይሆን የእናንተም እንዲሁ.... ቀልዴን አይደለም፡፡

ውድ ጓደኞቼ! የእስር ቤት የቅርብ ጓደኛዬ አባ ሰለሞን ቅዳሜ እለት አርፈዋል፡፡ በ68 ዓመታቸው በተኙበት እንዳሸለቡ ቀሩ፡፡ እስረኞች ሁሉ በአባ ሰለሞን ሞት በእጅጉ አዝነዋል፡፡ ቅርበት ያላቸው የእስር ቤቱ መርማሪ ፖሊሶችም ሳይቀሩ..... አባ ሰለሞን ግን ይኽን ዓለም ሕይወታቸው እስክታልፍ ድረስ ሲረግሟት ኖረዋል፡፡ "ለእድሜ ይፍታህ" ፍርድ ያደረሳቸው ወንጀል የፈፀሙት በስካር መንፈስ ተነሳስተው መሆኑ ሲታወሳቸው ይዘገንናቸዋል፡፡ በቅርቡ ከ15 ቀናት በፊት የሆነውን ላጫውታችሁ፡፡ እስረኞች አየር ለመቀበል ከአዳራሹ ቤታችን እየተጋፋን ስንወጣ፣ ባጋጣሚ እኔ ወደ ኋላ ቀረሁ፡፡ አባ ሰለሞን ትራስ በምታህል መተኛ ቦታቸው ላይ ስስ ብርድልብሳቸውን እንደለበሱ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ላይ ነበሩ፡፡ ጠጋ አልኩና በእጄ መታ መታ እያደረግኩ ስቀሰቅሳቸው "እ..... እ....." እያሉ ከተንጠራሩ በኋላ ".....ማነህ?" አሉኝ ...."ሮሲ..... ነኝ .... ሮሲ ....." አልኳቸው፡፡ ቀስ ብለው ወደ ቀኝ ጎናቸው ዘወር አሉና..... ድካም ያለበት ሳቅ ሳቁ.... "ምነው..... ምን አሳቀዎት አባ ሰለሞን.....?" አልኳቸው ".....ስምህ አሳቀኝ..... እናት አባትህ ልጄ ብለው..... ሻማ ለኩሰው ሮሲ ብለው እንዳልጠሩህ ታወቀኝ" አሉና ሳቃቸውን ደገሟት፡፡ ለራሴም ስሜን ደግሜ በልቤ ውስጥ ጠራሁት፡፡ "ነገር በአይን ይገባል" እንዲሉ ስሜንም በአይኔ አየሁት፡፡ ከዚያም አባ ቀጠሉ "ይህ ስምህ አንተነትህን ሸፍኖታል፡፡ ከዚህ ስምህ ጀርባ ያለው አንተነትህና እውነተኛው ባህሪህ አይዘማመዱም" አሉኝ፡፡ ንግግራቸው ሳይገባኝ ቀረና ዝም አልኩ.... "እውነተኛ ስምህን ማን ነበር ያልከኝ....?" አሉና ጠየቁኝ፡፡ አባን እንደ ፖሊሶቹ አልፈራሁም፡፡ በፍጥነት ነገርኳቸው.... "ፍሬዘር" አልኳቸው..... "ይኸውልህ! ከፍሬዘር ስምህ ጀርባ የሚያጠግብ ራዕይ አለ..... መልካም ተግባር ይታየኛል..." አሉና አይናቸውን ኮርኒሱ ላይ ተክለው በሃሳብ ተጓዙ..... አነጋገራቸው ውስጤ ዘልቆ ገባ፡፡ "ከሮሲ ስም ጀርባ ምን ይታይዎታል አባ?" አልኩ፡፡ ነብይነታቸውን ለማጠናከር ቀለል አድርጌ.... "ሮሲ አይገባም..... ባህል አይደለም...ስም ይሁን ግስ አይታወቅም... ከሮሲና ከእነዚህ መሳይ ቅፅል ስሞች ጀርባ ሁሉም አለ....." ሲሉ "አልገባኝም አባ!" አልኳቸው..... "ሽፋን ነው..... ስርቆት ማታለል.... ንጥቂያ.... ዝርፊያ..... ነፍስ ግድያ..... ሁሉም አለ ብያለሁ" አሉና ከተንጋለሉበት ፈጠን ብለው ተነስተው.... "ለነገሩ የዘመኑ ወጣቶች ለዕውቀትም ሆነ ለዕድገት እድለኞች ነበራችሁ፡፡ ግና ፈተና በዛባችሁ፡፡ የተፈጥሮም ችግር ጠናባችሁ፡፡ በኛ ጊዜ እንኳ የሌለ መድሐኒት አልባ በሽታ መጣባችሁ" .....አሉና ብርድልብሳቸውን እያራገፉ ጥለውኝ ወጡ፡፡ አነጋገራቸው ከመርማሪ ፖሊሶቹ የበለጠ ውስጤን አስፈራው፡፡ አእምሮዬ ማምለጥ በማይችልበት ውጥረት ታስሮ ምሬትና እንባ ተናነቀኝ፡፡ የራሴን የእናንተን የምወዳችሁን ጓደኞቼን ስምና ከስማችን ጀርባ ያለውን ማንነታችንን እፈትሽ .... እፈታ.... እቋጥር.... ጀመር፡፡ በዚህ አዳራሽ ሁሉም አይነት ሰው አለ፡፡ አዎ! ወጣቶቹ ይበዛሉ፡፡

CCRDA

ገብቶ ለተመለከተው "የሀገራችን ወንጀሎች በአብዛኛው የሚፈፀመው በወጣቶች ነው" ያስብላል፡፡ ግን እያንዳንዱን ወንጀል ነጥለንና ዘልቀን ከተመለከትነው የየራሱ ምክንያትና ውጤት ይኖረዋል፡፡ እስቲ አስቡት! እስከዛሬ እኛ የሰራናቸውን ወንጀሎች ለመፈፀም.... እናንተ አሁንም እያካሄዳችሁት ያለውን ወንጀል ለመቀጠል ምን አነሳሳን? ምን ገፋፋን? በጣም ቀላል ነው፡፡ ስለቸገረን.... ስለጠማን.... ስለታረዝን.... ቀምቶ፣ ነጥቆ፣ አጭበርብሮ፣ መኖርን መምረጣችን መሆኑ ነው፡፡ የሌሎችም ሌሎች ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል፡፡ የጤናና የትምህርት አለመስፋፋት፣ ከቤተሰብና ከማህበረሰብ ተለይቶ የራስን ህይወት ለመምራት ሲባል የወንጀል ማነቆ መሆን... ሌላም ሌላ.. አዝመራ እንኳን ከቤተሰብ ተለይተሽ ወደኛ ቡድን የተቀላቀለሽበት ምክንያት ይገባል፡፡ በንግዱ አለም ለአልኮል አሻሻጭነት ከድሀ ቤተሰቦችሽ ጉያ ነጥለው አምጥተው ለዚህ ስላበቁሽ ነው፡፡ አዎ! እኛ ሁላችን "በኢኮኖሚ፣ በጤና፣ በትምህርት እጦት ሳቢያ በተፈጠረ ውቅያኖስ ውስጥ የተጠነሰሰን የወንጀል ውጤቶች ነን" የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ፡፡ ግን ምን ይደረግ.....? እኛና እኛን መሰል ወጣቶች ከዚህ የወንጀል ባህር ውስጥ እንዴት ነው ዋኝተን የምንወጣው? ይህን ሁሉ እንድረዳ፣ እኔነቴን እንዳውቅ፣ ህሊናዬን የሞገትኝ አባ ሰለሞን ህይወታቸው ከማለፉ ከአንድ ቀን በፊት የመከሩኝ ነው፡፡ አባ ሰለሞን.... "ወጣት ነህ ይህ መንግስት ምህረት አድረጎልህ ነገ ልትፈታ ትችላለህ፡፡ እና! ላለፈው አንተነትህ አትቆጭ.... ራስህን፣ ወገንህን ሀገርህንም ለመርዳት አዲስ ሰው ሁን! እናትህ! አባትህ! ያወጡልህን ስምህን በአንተነትህ ተርጉመው፡፡ እውነተኛው ፍሬዘር ሁን" ነበር ያሉኝ.....

ወጣት ወንድማችሁ
ፍሬዘር ዘመኑ

CCRDA

“ወጣት የነብር ጣት”

በአሸናፊ ዓለሙ
ደረጃ አራተኛ

አንተ የተግባር ሰው የጥበብ አዋዩ
የዕድገት መሰላሉ ጮራው አስተዋዩ
የግኝት መዘክር መያጣ ሙዳዩ
እንዳቅም ለመኖር ሁሉን ነገር ቻዩ፡፡

ካለምክበት ሥፍራ ከወጠንከው ጎራ
ጎህ ሲቀድ ማለዳ እንደንብ ስትሰራ
ይመሻል..... ይነጋል.....

የህላዌን ሚስጢር የእስትንፋስን ድር
በእምነትና ዕናት፣ ፀዳልና ፍካት፣ ዛሬን ስታሰምር፡፡

ስታንፀባርቀው እንደ ጌጥ እንደ ወርቅ
ስታደማምቀው ፈርጥ ሆነህ ነጸብራቅ፡፡

የድህነት ዕልመት የቀርነት ድርሻ
በዕድሜ ትኩሳትህ ልትገፈው ስትሻ፡፡

የዜግነት ዕዳ በክንድህ ላይ ወድቆ
ወኔ፣ ምግባር፣ ጥረት፣ በውስጥህ ፈንጥቆ፡፡

ቅርሶችን በአደራ
ተፈጥሮን በጋራ፡፡
ማህበራዊ ጫና
ተንከባክበህ ጤና
የአስተሳሰብ ለውጥ እመርታ ህሊና፡፡

የጨለመው ሊፈግ
ሌሎች ያንተን ፈለግ
በጋራ ለማደግ
ልማት ሲፈክሩ...

የሰመረ ህይወት የዘለለህ ዕጣ
መባቻ መሰረት፣ የነገ በረከት፣ በድርሳን ሲወጣ፡፡

ሥራህ እንደ ፀሐይ
ከመቃብር በላይ

CCRDA

ለሰው ልጆች ሲሳይ።።
ህያው ውርስ ከትቦ
እንደ አደይ አብቦ።።
ዝባድ ሁኖ ሽቶ
ምድርን አንሰራፍቶ።።

የወገን ፍቅርን የጥልቀቱን ኬላ
ነጭ ላብ ንጣብህ የድካምህ መላ።።

ድርጊትህን አየሁ ደነቀኝ ዘንድሮ
ስትፈታ ሚስጢሩን የቅኔ ተፈጥሮ።።

CCRDA

ግብርና



በፍቱን ወርቅ

ብሩህ ተስፋ

በተሾመ ደስታ
ደረጃ አምስተኛ

ሰዓቱ መሽቷል፡፡ አበራ የጉሊት ነጋዴዎች ዕቃ አነሳስተው እንዳይሄዱ ይጣደፋል፡፡ ብዙም ሳይቆይ ጉሊት ደርሶ የሚገዛውን ገዝዝቶ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ ሲሆን ቤት ደረሰ፡፡ በውል እንኳ ያልተዘጋውን በር ገፋ አድርጎ ሲገባ “ማነህ.... አበርዬ ነህ?” የሚል የደከመ የእናቱ ድምፅ ነበር በቅድሚያ የተቀበለው፡፡ “እኔ ነኝ እማዬ! ተሻለሽ? መድሐኒትሽን ዋጥሽ?” ብሎ ከአጠገባቸው ተቀመጠ፡፡ “በሰላም መጣህ ልጄ” አሉና ትራሳቸውን አስተካክለው ሸርተት ብለው ጋደም አሉ፡፡ አበራ ከወለሉ ላይ የተከደነውን ሳህን ከፈት ሲያደርገው አይኑን ማመን አቃተው፡፡ ጠዋት “ለምሳሽ!” ብሏቸው ያስቀመጠው ምግብ ምንም ሳይነካ ቁጭ ብሏል፡፡ ድምፁን ለስለስ አድርጎ “እማዬ ለምድነው ምግቡን ያልበላሽው? ሐኪሙ እኮ! በደንብ መብላት አለብሽ ብሎሻል” አላቸው፡፡ “አይ! አበርዬ ትንሽ እኮ! በልቻለው” አሉት.... ፈራ ተባ እያሉ፡፡ ከተቀመጠበት አፍታም ሳይቆይ ተነስቶ፣ የከሰል ማንደጃው ላይ እሳት አቀጣጥሎ፣ በጥላሸት የጠቆረች ድስት አጣጥቦ በግርድፍ የተከተፈውን ሽንኩርት ጨምሮ ከእሳቱ ላይ ጣደው፡፡ ከዚያም የሀያ አምስት ሳንቲም ዘይትና በርበሬ... ውሃ... ሽሮ.... ጨው.... ጨማምሮ ሲበስል አወጣውና እናቱን ቀስቅሶ እራታቸውን እያጎረሰ አብልቶ ለሱም እንደነገሩ ቀማምሶ መድሃኒታቸውን ውጠው እንዲተኙ አደረጋቸው፡፡ ዕቃዎቹን አጣጥቦ ቤቱን ዘጋግቶ መደቡ ላይ ቁጭ ብሎ በዕለቱ የተማረውን ትምህርት ለጥቂት ሰዓታት ከልሶ ሲጨርስ፣ ከግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ፌስታል አወረደና ቁርጥራጭ የወረቀት ክምር አውጥቶ ይፅፍ ጀመረ፡፡ ያቋረጠውን ድርሰት....

ይህንን ድርሰት መፃፍ የጀመረው ገና የ11ኛ ክፍል የቀን ተማሪ እያለ ነበር፡፡ “ብሩህ ተስፋ” ያለው ይህ ረጅም ልብ ወለድ ድርሰቱን መፃፍ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ሲያቋርጥ፣ ሲቀጥል፣ ሲሰርዝ፣ ሲደልዝ፣ የፃፈው ሲጠፋ፣ መልሶ እንደ አዲስ ሲጽፍ በስንት ጊዜው ይኸው ወደ መቋጫው እያደረሰው ነው፡፡

ነፍሳቸውን ይማርና አባቱ ዘወትር እየጠጡና እየሰከሩ አምሽተው ገብተው ከእናቱ ጋር በረባና ባልረባው ነገር ብዙ ጊዜ ይጨቃጨቃሉ፡፡ የአበራ እናት “እኔ ለአንድ ልጄ ብዬ እንጂ የእሱ ንዝንዝና ንትርክ ሰልችቶኛል” ብለው ከቤት ከወጡ በኋላ ብዙ ጊዜ የሰፈር ሽማግሌዎች አስታርቀው አስገብተዋቸዋል፡፡ አበራ እናቱን ከመጠን በላይ ይወዳቸዋል፡፡ እሳቸውም እንደዚያው... አባቱ ሳንባቸውን ብርድ መቷቸው ብዙ ተሰቃይተውና ማቀው ነው ከሁለት ዓመት በፊት ይቺን አለም ትተው የተሰናበቱት፡፡ የእሳቸው መሞት እነ አበራን በቀን ጨለማ ውስጥ ቢከታቸውም፣ ለአባቱ ግን ትልቅ ግልግል ነበር፡፡ የአበራ አባት የወር ደመወዛቸውን ለቤተሰባቸው አምጥተው ከሰጡ በኋላ፣ ባለቤታቸው ናቸው እየመጠኑ ትንሽ የኪስ ገንዘብ የሚሰጧቸው፡፡ ከመስከርና ከመጠጣታቸው በስተቀር ደግና ሩህሩህ ሰው ነበሩ፡፡

ከሳቸው መሞት በኋላ ነው የነአበራ ኑሮ ምስቅልቅሉ የወጣው፡፡ የአባታቸው ጡረታም “አስር ዓመት በመስሪያ ቤቱ አላገለገሉም”ተብሎ ታገደ፡፡ በቤቱ ውስጥ እንኳን የሚበላ፣ የሚቀመስም በመጥፋቱ፣ የአበራ ዕጣ ፋንታ ከሚወደውና ከምንም በላይ ጊዜውን ከሚሰዋለት ትምህርቱ ተለይቶ ወደ ስራ ዓለም መሰማራት ሆነ፡፡ የኑሮ ጋሬጣን ሊዋጋ “ሀ” ብሎ በቀን ሰራተኝነት ተሰማራ፡፡ እናቱም ከእድራቸው የተሰጣቸውን ገንዘብ ቆጥበው ጉሊት የቸርቻሮ ንግድ ጀምረው ነበር፡፡ አበራ በቀን ሰራተኝነት የሚያገኛትን ገንዘብ ከእናቱ ጋር አዳብለው፣ የወር ቀለባቸውን እንደ ነገሩ ችለው፣ የተረፋቸውን እናቱ ጋር ያስቀምጣሉ፡፡ አሁን ደግሞ ይኸው እግዚአብሔር ይመስገን ከዚያ የተሻለ የአናፂነት ስራ በማግኘቱና ደመወዙም የተሻለ ስለሆነ፣ ያቋረጠውን ትምህርት በማታው ክፍለ ጊዜ ቀጥሏል፡፡ በዕረፍት

CCRDA

ቀኑም በግሉ የተለያዩ ወንበሮችን፣ ጠረጴዛ..... የመሳሰሉትን በየሰው ቤት እየተዘዋወረ መስራቱን ተያይዘታል። በሚያገኛት ገንዘብም ለወር ቀለብ፣ ለት/ቤት፣ በተረፈችውም አንዳንድ የአናፂነት ዕቃዎችን መዶሻ፣ መጋዝ፣ መላጊያ.... የመሳሰሉትን እየገዛ ያስቀምጣል።

አበራ እንዲህ ሀሳቡን ሙሉ በሙሉ አሰባስቦ፣ ትምህርቱን እየተማረ፣ ስራውን እየሰራ ባለበት ወቅት ከባድ ፈተና ገጠመው። እናቱ ታመው አልጋ ላይ ዋሉ። ጊዜ ሳይፈጅ ከወር እስከ ወር እየቆጠበ ለችግር ጊዜ እያለ የሚያሰቀምጣትን ገንዘብ ሰብስቦ ወደ ሐኪም ወሰዳቸው። ብዙ ብር ጨርሶ ይኸው እስካሁን እያሳከማቸው ነው። አሁን ግን በደህና ጤንነት ላይ ይገኛሉ። አበራ በህክምናው ብዙ ገንዘብ በማውጣቱ ምንም ያህል አልተሰማውም። "እናቴ ጤናዋ ይመለስላት እንጂ.... ገንዘብን በወጣትነት ላቤ ሰርቼና ለፍቼ አገኘዋለሁ" ይላል ለራሱ.....

በቅርቡ የጀመረውን ትምህርት ለማጥናት በቂ ጊዜ ባይኖረውም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያጠናል፣ ይጥራል፣ ይተጋል፣ በወጣትነቱ ኑሮን ለማሸነፍ ደፋ ቀና ይላል። እግዚአብሔር ያሳካለት እንጂ ሐሳቡማ! ብዙ ነው። መቼም የተመኙትን ሁሉ ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም፣ አበራ ግን የሚናገረውን የሚያስተውል፣ የሚሰራውን የሚያውቅ፣ የአቀደውን በተግባር ላይ የሚያውል ታታሪ ወጣት ነው። እናቱን ጤና ከሰጠለት ደግሞ ውጥኑ፣ ዕቅዱ ብዙ ነው። የሚያገኛትን ገንዘብ የወር ቀለባቸው፣ የመብራት፣ የውሃ ክፍያን አስችሎ፣ በወር አንድ ጊዜ ለሚከፈል ዕድር፣ በመስሪያ ቤት ካሉት ጓደኞቹ ጋር ለገባው እቁብ መድቧታል፣ በግሉም እንጨት ገዝቶ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ረከቦት የመሳሰሉትን ለመስራት፣ ትምህርቱን በደንብ አጥንቶ በቀጣዩ ዓመት የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ፣ የጀመረውን ድርሰት ጨርሶ ለማስጠረዝና ወደፊት ለማሳተምም አቅዷል። ሀሳቡ ከተሳካለት ዕቅዱ ከሰመረለት....

እኩለ ሌሊት ሆኗል። አበራ አሁንም መደቡ ላይ ቁጭ ብሎ ይጽፋል። ድንገት እናቱ ከእንቅልፋቸው ብንን ብለው "አበርዬ ሊነጋ አይደለም እንዴ? ተኛ እንጂ....." ሲሉት "እሺ! እማዬ ትንሽ ቀረችኝ..... ይቺን ጨርሼ እተኛለሁ። አንቺ ተኚ!" አላቸው። ብዙም ሳይቆይ ድካምና እንቅልፍ ስለተጫጫነው ወረቀቶቹን ሰብስቦ ድካሙን በእንቅልፍ ሊወጣ ከእናቱ ጎን ጥቅልል ብሎ ተኛ።

CCRDA

አኩሪ ገድል ስራ

በዮናስ ወልደየስ
ደረጃ አምስተኛ

የማስተዋልን መነፅር አጥልቄ ከውስጥ ልቦናው ዘልቄ
የምኞቱን ድምፀት ናፍቄ.... ከአፅምሮው ጓዳው ሽምቄ፡፡
ሹክ ሲል ወገን ሰማሁት.... የልቡን ምስጢር አደመጥኩት
ራዕይ ሕልሙን አየሁት....ጉጉት ምኞቱን ቃኘሁት፡፡
እድገት ይላል ወገኔ.... ሲያልም ያድራል ስልጣኔ
የአደራው ቃል ብያኔ.... ለካስ ወድቋልና በእኔ!

ለሰንደቅ አላማ ልፅልና.... ለትንሳኤው እድገታችን ፍፅምና
እንዲያገግም ታሪካችን እንደገና.... አኩሪ ገድል ልፅፍ በብራና
የትውልድ ቃል ጎሕ ፋና... አደራው በእኔ ወድቋልና!
የነገይቱ ኢትዮጵያ እጣ ፈንታ... ዛሬ በስብዕናዬ ገበታ
ተነስ! ስትል ለግንባታ..... ንቃ! ስትል አሰምታ፡፡

በእልፍ..... አእላፋት ወገን እንባ..... የወጣት ልማት ጥሪ ስብሰባ
ከፅንፍ ፅንፍ.... ከአድማስ አድማስ..... ሲያስተጋባ፡፡
አለሁ ልላት ለአገሬ.... ልታደጋት ከድህነት ነገም ዛሬ፡፡
ለብዙሀኑ ወጣት ጉስቁልና... ለከተመው ቤቴ ብሎ በጎዳና ለመፍትሔው ለመዳኛው ሕክምና... ላለማወቅ መጋረጃ ድንቁርና
ለወደፊቱ ሕይወት ዋስትና..... ለካስ እኔው ነበርኩና!

እናማ! ወገን! ኢትዮጵያ ልትለማ እግሯ ሲያንሰራራ
ለተተኪው ትውልድ መሰረት አኑራ
ጎበዝ እርዳኝ ስትል እናት ስትጣራ
ጥሪዋን ተቀበል..... አኩሪ ገድል ስራ፡፡

የማንነትህ እምቅ ችሎታ..... የስራ ፈጣሪነትህ ስጦታ
ገሀድ አውጥተህ በአፍታ.... ለምጣኔ እመርታ፡፡
የአስተዋይነትህ ውብ አርማ.... በምልዓተ ዓለም ሲሰማ
ፍንትው ሲል ቃል ኪዳኑ... የጨለማው ችካል ካስማ፡፡
አንተ ልጇ ስትደርስላት.... የችግር ቀንበር ልትንድላት
የስልጣኔውን ዜና ብስራት.....በላብህ ለውጠህ ልትቸራት
ያነባችውን መሪር እንባ..... በእድገትህ አራምደህ ልትክሳት፡፡
በአበው ቃል አደራ....የእድገት ጋሬጣ ሳትፈራ
ስለ ሕዝብና ባንዲራ.....ወጣቱ ሰልፈኛ አኩሪ ገድል ስራ፡፡

CCRDA

ከልመና ውጣ



በዳዊት አስፋው

እድለኞቹ ትውልዶች

በዮሴፍ ሸዋንዳኝ
ደረጃ ስድስተኛ

ወጣቶች እምቅ ችሎታን፣ አዲስ የፈጠራ ሃሳብን፣ ደፋርነትን፣ አሸናፊነትን፣ ብልሃትን፣ ፍልስፍናን፣ በራስ መተማመንንና በትኩስ ሀይል የመስራት ፍላጎትን በአንድ ላይ አጣምረው የያዙ ናቸው።።

እውነተኛው ዕድገትና ለውጥ እንደሚመጣ የሚታሰበው በወጣቶች ነው።። ወጣቶች ለስራ ካልተነሳሱ ህዝቡ በሳይንስም ሆነ በማህበራዊው ኑሮው እድገትን ሊያገኝ አይችልም።። ወጣቶች በጭንቅላታቸው ውስጥ የተከማቹትን ዕውቀቶችና ችሎታዎች በተግባር ለማዋል ሰላም፣ ምቹ የስራ ጊዜና መማርን አጥብቀው ይሻሉ።። ይህ ደግሞ እውን ከሆነ ዓመታት ተቆጠሩ።። ዛሬ ወጣቱ ምንም ለሕይወቱ የሚያሰጋው ነገር ባለመኖሩ ምንጊዜም የሚያስበው የተሻለ ሰርቶ የራሱንና የህብረተሰቡን ኑሮ ለመለወጥ ነው።።

ከዚህ የተነሳም ከከተማ እስከ ገጠር በፈለጉት የሙያ መስክ ተሰማርተው እያገለገሉ ይገኛሉ።። በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወጣቱ ትውልድ በብሔራዊ ልማት ከፍተኛ ተሳትፎ እያሳየ ይገኛል።። ገበሬው ከጓላ ቀር አስተራረስና የአሰራር ዘዴ ተላቆ፣ በዘመናዊው ስልት እንዲጠቀም በግብርና ሙያ የሰለጠኑ ወጣቶች ከጎኑ ሆነው አስፈላጊውን ምክርና እርዳታ ያደርጉለታል።። ከእጅ ወደ አፍ የነበረው ምርቱም እጥፍ አድጎለት የራሱን ኑሮ ከመለወጥ አልፎ ለተቀረው የህብረተሰብ ክፍል አለኝታ እንዲሆን አስችሎታል።። ከህክምናና ከትምህርቱም አንፃር ያየነው እንደሆነ በሙያው የሰለጠኑ ወጣቶች ሳይሰላቹ የቤተሰቡንና የልጆቹን ጤና እንዲጠብቅ እያስተማሩት፣ ለተሻለ ህይወት እንዲበቃ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያበረከቱ ናቸው።።

በኢንዱስትሪዎችና በፋብሪካዎችም ውስጥ ወጣቱ እያበረከተ ያለው አገልግሎት በቀላሉ የሚገመት አይደለም።። በተለይም የቀሰመውን እውቀት ከፈጠራ ስራው ጋር በማቀናጀት የተለያዩ የፋብሪካ ውጤቶችንና መለዋወጫዎችን በራሱ ጥረት በመፈብረክ ላይ ይገኛል።። ፋብሪካዎቹም የማምረት አቅማቸው ከፍ ከማለቱም በተጨማሪ ወጣቶቹም ለተሻለ የፈጠራ ስራ ፍላጎታቸው ተነሳስቷል።። ወጣቶች ዛሬ ተፈጥሮ የለገሳቸውን የፈጠራ ችሎታ በልምድ በማገዝ ለሀገራቸው መኩሪያና ዕድገት ፈር ቀዳጅ ሆነው መልካም ፍሬ እያፈሩ ይገኛሉ።። ወደፊትም ቢሆን የበለጠ የፈጠራ ችሎታቸውን በማዳበር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ መገንባት ይጠበቅባቸዋል።። የህዝቡም ኑሮ ሊለወጥ የሚችለው ወጣቱ ጠንክሮ ሲሰራ ብቻ ነው።።

አሁንም ገና ከወጣቱ የሚጠበቅ አለ።። በህክምናው፣ በሳይንሱ በእርሻው፣ በምህንድስናውና በሌሎችም የሥራ ዘርፎች ገና አልተሰራባቸውም።። ብዙ ችሎታዎችንና ፈጠራዎችን የሚጠይቁ ናቸው።። ይህን እምቅ የፈጠራ ችሎታ አውጥተው በተግባር ላይ እንዲያውሉት ደግሞ የሚያሰራቸውና የሚያበረታታቸው ረዳት ያስፈልጋቸዋል።። ይህንንም ካገኙ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ለአለም ህብረተሰብ የሚጠቅም አዲስ ግኝት የማይፈጥሩበት ምንም ምክንያት አይኖርም።።

ትክክለኞቹ ወጣቶች የራሳቸውን መብትና ጉዳይ ከመጠየቃቸው በፊት ተግባራቸውንና አገልግሎታቸውን ያስቀድማሉ።። ተግባርን መፈጸምና መጠየቅ ደግሞ ጎን ለጎን የሚጓዙ ናቸው።። በመሆኑም ያገኙትን አጋጣሚና ዕድል በመጠቀም ከራሳቸው አልፈው ወገናቸውንና ሀገራቸውን ለመጥቀምና ለመገንባት እየጣሩ ይገኛሉ።። ብዙዎቹ ወጣቶች በአሁኑ ጊዜ በግልም ሆነ በጋራ በመደራጀትና በመስራት ራሳቸውን ለውጠዋል።። የተቀሩትም ቢሆኑ በማህበራት በመሰባሰብ መንግስትና አንዳንድ ድርጅቶች ለዕድገት የሚያሳዩትን ትጋትና ጥረት ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የማቴሪያልና

CCRDA

የስልጠና ድጋፍ ስለሚያደርጉላቸው ለአመታት ስራ ፈተው የነበሩ እጆች በስራ ተጠምደዋል፡፡ ስለዚህም ወጣቶቹ ዛሬ በራስ የሚተማመኑና ለሀገር ለወገን ተቆርቋሪ ዜጋ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ወጣቶች በየቤታቸውና በየመንገዱ እጃቸውን አጣጥፈው በመቀመጥ ከሰማይ መና እንዲወርድላቸው ይመኛሉ፡፡ ሥራ ራሱ ፈልጓቸው ቤታቸው ድረስ ቢመጣ ፍፁም ደስተኞች ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳም ወርቃማውን ጊዜያቸውን በከንቱ እያሳለፉት ይገኛሉ፡፡ መጨረሻቸው ደግሞ የሀገርና የወገን ሸክም ከመሆን አያልፍም፡፡

በየትኛውም የአለም ክፍል ብንመለከት ስማቸው ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የተናኘው ታላላቅ ሰዎች በራሳቸው ጥረትና ድካም ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው ጠንክረው በመስራታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች “አንቱ” ለመባል የበቁት ሌት ተቀን ስለሰሩ እንጂ ቤታቸው ተቀምጠው ስራ ፈልጓቸው ወደ እነሱ እንዲመጣ በመናፈቃቸው አይደለም፡፡ በሀገራችንም ስለ ልብ ወለድ ድርሰት በተነሳ ቁጥር ስማቸው ከስራቸው ጋር ትላንትም ሆነ ዛሬ፣ ገና ወደፊትም ሲጠራ የሚኖረው ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ገና በወጣትነታቸው ዘመን ነበር ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ስራ ያከናወኑት፡፡ ስለሆነም ያሁኖቹ ትውልዶች ደግሞ በየትኛውም ጊዜ ከኖሩት የተሻለ ዕድለኞቹ ትውልዶች ናቸው፡፡ ወጣቱ ባለፈው ጊዜ ሁሉንም መመለስ አይችልም ነበር፡፡ ጤና ብናጣ በሕክምና ልንመልሰው እንችላለን፣ ገንዘብ ብናጣ ሰርተን እናገኛዋለን፡፡ አንዴ ያመለጠን ዕድል ግን እስከ ዕድሜ ልካችን በፍፁም ለማግኘት አንችልም፡፡

ስለሆነም ዛሬ በእያንዳንዱ ወጣት እጅ ምንጊዜም የማይገኝ ዕድል አለ፡፡ ይሄውም የማጥናት፣ የመማር፣ የመመራመር፣ የመፍጠር፣ የመፈላሰፍና የመስራት ዕድል ነው፡፡ ስለዚህ ያገኙትን አመቺ ጊዜና ዕድል በመጠቀም፣ ይህን አጭር የወጣትነት ዘመን በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል፣ ታሪክ የማይረሳው ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ነገር ሰርቶ ማለፍ፣ የእያንዳንዱ ወጣት ሃላፊነትና ግዴታ ነው፡፡

CCRDA

“ሕይወት..... ኑሮ..... በወጣቶች”

በእየሩሳሌም ብርሃኑ
ደረጃ ስድስተኛ

ድንገት እደተዘራ..... ወፍ ዘራሽ እንቡጥ ፍሬ፣
እንደሚወለድ ሳይፈልጉት..... የጨለማ ዓለም ድብቅ አውሬ።።

ሕይወት በዕድል ተወስና.....፣
ሰው ለመባል ተወጥና.....።።

መወለድ ማደግ ዝም ብሎ፣
በነገ ተስፋ ራስን ጥሎ።።

አባት እናት እህት ወንድም..... ማሰብ ሳይኖር ማሰላሰል፣
ራስን ለዛሬ ለማቆየት..... መውጣት መውረድ መንጠላጠል።።

ሲገኝ በስራ ራስን ጠምዶ.....፣
ላለመውደቅ ተሽመድምዶ.....።።

አሊያም .... ለማደር ሲባል የዛሬን ቀን፣
ለልመና ይዘረጋል..... እጅ ወደ ላይ በሰቀቀን።።
የተገኘን አፍ አላምጦ.... ሆድ ከሞላ ምንቸገረ፣
መኖር አይደል የሚፈለግ.... ዕድሜ ሰጥቶ ከተኖረ?

የመማር ሞራሉ ወድቆ..... ለመስራት ፍላጎት ሲያጣ፣
አመል አይኑን ሲገልጽና..... ቦዘኔነት ገሀድ ሲወጣ።።
ጉንጭ በጫት ተወጥሮ.....፣
ከንፈር በሲጋራ ጭስ አሮ.....።።
ሲማረር በመቸገሩ፣
ቀን ሳይሞላ በመፈጠሩ።።

ድንገት ወድቆ እንደበቀለ..... ለምለም ፍሬ ወጣትነት
ሐረግ ሆኖ ላይሸፍናት..... መጽደቅ ላይኖር በአበባነት።።
ሊረጋገጥ በያለበት..... ህይወት ስትሆን የሜዳ ሳር፣
ወጣትነት እንቡጥ ፍሬ..... ሕልም..... ተስፋ..... ሆኖ ሲቀር።።

በምኞት ዓለም..... በሀሳብ አምባ፣
ወጣትነት..... ደረቅ እንባ.....!!

CCRDA

እስኪ ነጋ



በኢሳያስ ከበደ

ወጣትነት በራሱ

በአልአዛር በቀለ
ደረጃ ሰባተኛ

ወጣትነት በራሱ፣ ሮጠ የማይደክምበት፣ ሠርቶ የማይጠገብበት፣ ሰቆ የማይበራበት የእድሜ ክልል ነው፡፡ ወጣትነት ትምህርት ቤት ገብቶ መደበኛ በሆነ የመማር ማስተማር መርሀ ግብር እውቀትን ማዳበር፣ በተፈጥሮ የተቸሩትን ልዩ ችሎታ ከተሻለ ደረጃ ላይ ማድረስና በተግባር ማዋያ ጭምር ነው፡፡ ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ወጣቶች እንደማናቸውም የአለም ወጣቶች ከትምህርታቸው ጎን ለጎን የተፈጥሮ ክህሎታቸውን ለማዳበር ሌት ተቀን ደፋ ቀና ሲሉ የሚውሉት፡፡

እውቀት ተተግብሮ በአይን ሊታይ ወይም በእጅ ሊዳሰስ ካልቻለ፣ እምቅ ሆኖ ይቀራል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን እምቅ ችሎታ ገሀድ ለማውጣት የተለያዩ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች አለመሟላት ምክንያት የኢትዮጵያ ወጣቶች ያሏቸው የስነጽሁፍ፣ የስነስዕል፣ የቅርፃቅርፅና የተለያዩ የእጅ ሙያዎቻቸው ለብዙ ዘመናት እምቅ ችሎታዎቻቸው ሆነው እንዲቆዩ ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጅ ዛሬ ዛሬ ወጣቶች በማህበር በመደራጀት ስራዎቻቸውን በአዳራሾች፣ በኢግዚቪሽን ማዕከሎችና በሌሎችም ስፍራዎች በማቅረብ የሚያደርጉት ችሎታን የማንፀባረቅ ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡

ከዘመን ዘመን፣ ከቦታ ቦታ አገርና ህብረተሰብ ከወጣቱ ትውልድ ብዙ ነገር ይጠብቃሉ፡፡ ሁለንተናዊ አስተዋጽኦም እንዲያበረክት ይገፋፉታል፡፡ የኢትዮጵያም ወጣቶች ይህንን የአገር ግዴታ ጥሪ በተመለከተ በተለያየ መልኩ ሲወጡት እናያለን፡፡ ካያት ከቅድመ አያት ሲተላለፍ የመጣላቸውን የአገር ደህንነት ይጠብቃሉ፡፡ መንገድ በሌለበት ንፁህ ውሀና መብራት በማይታሰብበት የሀገሪቱ ጓላቀር ክልሎች ድረስ ዘልቆ በመግባት በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ፊደል መቁጠር የሚችግረውን ወገናቸውን በማስተማር እንደድባብ በላያቸው ላይ የተዘረጋውን የማይምነት ጥላ ለማስወገድ በተምሮ ማስተማር ዘመቻ ይካፈላሉ፡፡ በቀይ መስቀል ማህበር ራሳቸውን በማደራጀት ያለምንም ጥቅም ፍለጋ፣ አደጋ በደረሰበት ስፍራ ሁሉ እንደወፍ በሮ በመድረስ በአቅማቸው የመጀመሪያ እርዳታ ሲሰጡ ይታያሉ፡፡

ኢትዮጵያ አገራችን ታዳጊ ከሚባሉትና በዓለም ካሉ ድሃ አገሮች አንዷ እንደመሆኗ መጠን፣ ወጣቱን የሚያሳትፍ የልማት መስኮች ውስንነት ከአመት አመት ቁጥሩ ባያሌ እየጨመረ የሚሄደውን ወጣት ለማስተናገድ አልቻለም፡፡ ይህም በመሆኑ የመንፈስ ደካሞች ለሆኑና የሌላን እጅ በመጠበቅ ራሳቸው በራሳቸው ስራ ፈጥረው ለመንቀሳቀስ ለማይሞክሩት ሰነፍ ወጣቶች የዋልጌነት በር ከፍቷል፡፡ ለጫት፣ ለሲጋራ፣ ለሀሽሽና ለመሳሰሉት ከራሳቸው አልፎ ህብረተሰቡን ለሚጎዱ ሱሶች ተጋልጠዋል፡፡ በዚህ መልኩ ይህ የሕብረተሰብ ጠንቅ የሆነው ሱስ ሥር ሰዶ እንዳይቀጥልና ወጣቱም ውድ ጊዜውን በመጥፎ ድርጊት ላይ እንዳያባክን መንግስትና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች የበኩላቸውን ጥረትና እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በውል ተረድተው ሊያስቡበት ይገባል፡፡

ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች በተወሰኑ የወጣቱ ክፍሎች እለታዊ ኑሮ ውስጥ ጎልተው የሚታዩ ቢሆንም ከዚህ አልባሌ ድርጊት ውጭ ራሱን ጠብቆ የሚኖረው ወጣት ቁጥር እንደሚበልጥ ግን አያጠያይቅም፡፡ ሱሶችን ከህይወት ውጣውረድ እንደመሸሸጊያ በማድረግ ፋንታ ራሳቸውን በማደራጀትና የሙያ ማህበራትን በማቋቋም ያላቸውን እምቅ ችሎታ ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት ለኢትዮጵያ ወጣቶች ለአስተዋይነት በማስረጃነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ለዚህም አባባል የወቅቱን አንገብጋቢ በሽታ ከመቋቋምና ስርጭቱን ከመቆጣጠር አኳያ ከትምህርት ቤት ጀምሮ በየመንደሩ ያለስራ የሚውሉ ወጣቶች በመሰረቱት የፀረ ኤድስ ክበብ አማካይነት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከምንም በላይ ለአስተዋይነታቸው ማስረጃ ነው፡፡

GCRDA

ትኩረት ለወጣቱ

በታየልኝ ጌታነህ
ደረጃ ሰባተኛ

ሠው ከሠው ተፈጥሮ ሲኖር በዚህ ዓለም፣
እንደ መረዳዳት፣ እንደ መተባበር፣ የሚያስደስት የለም።።

የመኖር ዘይቤው ውጥንቅጡ ጠፍቶት፣
ተፈጥሮ ተጭኖት ድህነት አራቁቶት፣
ማጣት ጎረቤቱን በጉያው ታቅፎት፣
የሚኖር ስንት አለ እናንተው ፍረዱት።።

አንዳንዱ ጎበዝ ነው ለሥራ የተጋ፣
ጎህ ሲቀድ ተነስቶ ገና ሲነጋጋ፣
የተከፈተውን ጉሮሮ ሊዘጋ፣
በጠዋት ይነሳል ስራውን ፍለጋ።።

አንዳንዱ ደካማ የደነዘዘማ፣
በጫት በሲጋራ ልቡን እያደማ፣
ቁማሩን ሲቆምር በቀን በጨለማ፣
ሕይወቱ ይኸው ነው ምን ይሥራ ሌላማ!

ኑሮን ኖርኩ ይላታል እኔን መኖር ያርገኝ፣
ሲፈጠር ጀምሮ፣ ምንም ሳይሻሻል፣ እዛው ቆሞ ሲገኝ።።

ቢሰራ ቢደክም ላቡን አንጠፍጥፎ፣
መኖር ይችል ነበር ኑሮን አሸንፎ፣

ያየውን አጢኖ፣ የራሱን ፈጠራ፣ ደምሮ ጨምሮ፣
እሱ የሚያውቀውን ለቀሪ አስተምሮ፣
ቢሰራ ይህ ወጣት ከንዱን አስተባብሮ፣
መድረስ ይችል ነበር ከደልቃቃው ኑሮ።።

መስራት የመረጠ ቆርጦ የተነሳ፣
አስተዋይነትን ፈጠራን ያልረሳ፣
መስራትን ሳይቆጥር ከጭንቅ ከአበሳ፣
አለ ብዙ ወጣት፣ ለፈጠራ ስራ ልቡን ያነሳሳ።።

ፊት ካላዞሩበት ካሳዩት መንገድ፣
ወጣቱ ይሰራል ሁሉን አንድ በአንድ።።ተቃንቶ እንድናየው የነገ ሕይወቱ፣
በቅድሚያ ይሰጠው ትኩረት ለወጣቱ።።

CCRDA

ወጣቱና ችሎታው



በዘላለም ተረፈ

መቅረዝ

በቀለሚ ወርቁ
ደረጃ ስምንተኛ

ወጣቶች የቀደምቶች ተረካቢ፣ የተተኪው ትውልድ ድልድይ በመሆን የላቀ ድርሻን የማበርከት ሃላፊነት አለባቸው። ወጣትነት ትኩስ ጉልበት፣ ድፍረት፣ የሰላ አዕምሮና ዕውቀት ያቀፈ የዕድሜ እርከን ነው። በመሆኑም ወጣቶች ከዚህ የዕድሜ ዘለላ ማበርከት የሚገባቸው አያሌ ጉዳዮች አሉ።

የምንገኘው በሶስተኛው ዓለም አገር ነው። ኑሮአችንም ከእጅ ወደ አፍ ወይም ከመሞት መሰንበት ዓይነት ነው። ድህነታችንን አንጋጠን እየተመለከትን፣ ከታች መሆናችንን በማሰብ፣ በምቾት የሚደላቀቁትን ከእኛ ጉስቁልና ጋር ማነፃፀሩ ለወጣቱ የሚፈይደው ነገር የለም። ያለንን ልዩ ተሰጥኦና ዝንባሌ በማውጣት፣ ለወገን በሚጠቅም መልኩ መስራት ከወጣቶች ይጠበቅብናል። ፈጠራችንን በስራ ላይ ልናውለው ይገባል። ብዙ ወጪ በማይጠይቁና በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉ ቁሳቁሶች ብዙ ሥራዎች ብንሰራ በራሳችን እንድንተማመን ያደርገናል።

ለምሳሌ በቅርቡ አንድ ኢትዮጵያ ወጣት ራዲዬ መስራቱና ግኝቱን ለተማሪዎች ማስታወቁ አንድ እመርታ ነው። በአንድ ወቅትም የሸክላን ውጤት እንደ ማቀዝቀዣ /ፍሪጅ/ መጠቀም እንደሚቻል የታየበት ጊዜ ነበር። ይህ የወጣትነት ፈለግ ኑሮን በዘዴና በቁጠባ፣ አመለካከትን በስፋትና በጥልቀት፣ ዕውቀትን በተግባር ላይ የሚያውል የፈጠራ ደብር ነው። በሌላም በኩል ወጣቱ ተፈጥሮን በመንከባከብ፣ ታሪካዊ ቅርሶችን በመጠበቅ፣ በመመልከትና የሱንም አሻራ በማኖር፣ ህይወቱን፣ የትላንት ማንነቱንና የዛሬ እርሱነቱን ማለምለም አለበት።

አንድ ነገር ላይ ትኩረት ለማሳረፍ መነሻ ያስፈልጋል። የልማት ድርጅቶች በሚፈጥሩት በኤክስቴንሽን ፕሮግራም በመታቀፍ በምግብ ራስን ለመቻልና አልፎ ተርፎም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ወጣቱ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይገባዋል። በማህበራዊ ኑሮ ዘርፍም ህብረተሰቡ በሚፈልጋቸው ጥቃቅን በሚመስሉ ግን የገዘፉ ችግር ላይ በመካፈል መፍትሔዎችን መፈለግ ወሳኝነት አለው። ለምሳሌ ብዙ እናቶች ወሊድን ለማራራቅና እርግዝናን ለመከላከል እየፈለጉ የቤተሰብ ምጣኔ ዘዴዎችን ባለማወቃቸው ለችግር ይጋለጣሉ። ይህ እንዳይሆን በተወሰነ አካባቢ ጽህፈት ቤቶችን በማቋቋም ስለስነ ሕዝብና ስለ ጤና ጠቀሜታ ወጣቱ ማስተማር አለበት።

ሌላም አለ። ሕብረተሰቡ በአብሮ መኖር ዙሪያ የኑሮ ሰንሰለት ውስጥ የፈጠራቸው እጅግ ጠቃሚ ማህበሮች አሉ። ለምሳሌ ዕድር..... በሞት ጊዜ ብቻ ሳይሆን የኑሮ ጫናና ፈተና ለጎዳቸው፣ በህይወትና በሞት መካከል ላሉ አባላቱ እርዳታ እንዲያደርግ ማስቻል አንዱ ነው። በተጨማሪም አቅም በማጣት የሚበተኑት ዕድሮች ህልውናቸውን እንዳያጡ ከሌላ ዕድር ጋር እንዲዋሃዱ ማድረግ፣ ጥሩ ካፒታል ያላቸው ደግሞ ትርፋማ ሊሆኑ በሚችሉበትና የኢኮኖሚ ዕድገት በሚያመጡ የሥራ መስኮች ላይ እንዲሳተፉ አመቺ ሁኔታ መፍጠር ወጣቱ ሊካፈልባቸው ከሚችሉ ሥራዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

ሥራ አጥነትን መሠረታዊ ምክንያት አድርጎ፣ ክቡር ጊዜን በዋል ፈሰስ ከማሳለፍ ይልቅ ሥራን የመፍጠር ልምድን ማዳበርና በተገኘው መስራት፣ ለትምህርት፣ ለጤናና ለመሳሰሉት ድርሻን ለሚጠይቁ ጉዳዮች መተባበር፣ ወጣትነት ከሚወቀሰባቸው ጎጂ ባህርያት ወይም ልምዶች ራስን መጠበቅ፣ መግዛትና መቆጣጠር፣ ወጣቶች ለሃላፊነት ብቃት እንዳላቸው ማስመስከርና ህይወትን በተግባር እየኖሩ ለሌላው አርአያ መሆን አለባቸው። ወጣቶች በጊዜ ዙርያ ገብ፣ በድንበር ከለላ የማይወሰኑ ኗሪ መቅረዞች ናቸውና።

CCRDA

ዳግማዊ ወጣት

በአክሊሉ ብርሃኑ
ደረጃ ስምንተኛ

የአፍላነት ቋጠሮ.....ጉልበት ትኩሳቱ
ጠብቆ ተተኪ..... የቅርስ አብነቱ
አርአያ ፍጥረቱ.... ወጣቷ..... ወጣቱ፡፡

መሠረት ለሚሆን እጅግ ወሳኝ ስራ
ሀገርን በማልማት ወገን እንዲኮራ
የእድገት ሰፊ ጅረት የትውልድ አዝመራ፡፡

ውበት ዕውቀት ሆኖ በተግባር ለመርካት
ሥጋት ላይሆን ሽበት እንባ ላይሸመት
የቃሉ ምስጢር ነው ጥረት በልጅነት
ዳግም ወጣትነት፡፡

የአፍላነት ቋጠሮ..... ጉልበት ትኩሳቱ
ጠብቆ ተተኪ..... የቅርስ አብነቱ
አርአያ ፍጥረቱ..... ወጣቷ ወጣቱ፡፡


የእዳሪውን ችግር እንባ ላይ ጋርደው
ሆደ ባሻ ወገን ላየታይ በቀዬው
ወጣቱ ደረሰ ሸተተኝ መዓዛው፡፡

በዘመነ ልማት በንጋት ተስፋችን
በለኮስነው ሻማ በዕውቀት ትጋታችን
ለግብራችን ዕድገት ልማት ላገራችን
ፍቅራቸው ሆኖ ዕዳ ሀገር ላወረሱን
በበጎ ሥራቸው ለዚህ ላደረሱን
ጠብቀን እንኑር የሕላዊ ደርዙን
የአደራ ቅርሱን፡፡

የአፍላነት ቋጠሮ ጉልበት ትኩሳቱ
ጠብቆ ተተኪ የቅርስ አብነቱ
አርአያ ፍጥረቱ.... ወጣቷ..... ወጣቱ፡፡

ECRDA

ተስፋ በጥረት ሲታገዝ



CRDA

በጎይለልዑል ብርሃኔ

በብሔራዊ ልማት የወጣቶች ሚና

በትሁን ጎሹ
ደረጃ ዘጠነኛ

የኢትዮጵያ ወጣቶች ከሚጠበቅባቸው ሃላፊነት አኳያ በብሔራዊ የልማት ዘርፍ በኩል ብዙ ሚና ሊጫወቱ ይገባል። በአሁኑ ሰዓት በብሔራዊ ልማት ተንቀሳቃሽነቱ በጥሩ አብነቱ ሊጠቀስ የሚችል ቢኖር የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ቅርስ ባላደራ (Ethiopian Heritage Trust) ነው። በዚህ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ቅርስ ባላደራ በተሰኘው ድርጅት ውስጥ ብዙ ወጣቶች በበጎ ፈቃደኝነት ተነሳስተው ብዙ የብሔራዊ ልማት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በዚህ ብሔራዊ የልማት ድርጅት ውስጥ ወጣቶቹ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል፣ በዕንጦጦ ዙርያ አካባቢ መንግስት ለድርጅቱ በፈቀደው ሰፊ ክልል ውስጥ የተመናመኑና የጠፉ አገር በቀል ዛፎችን እንደቀድሟቸው ለመመለስ ጥረት ማድረግ ነው። በዚህ እንቅስቃሴ ብዙ ወጣቶች የተግባር ተሳታፊ በመሆን በርካታ የዛፍ ችግኞችን ተክለዋል። ይህ የዛፍ ችግኝ ተክል ፕሮግራም ከድርጅቱ አላማዎች አንዱር እንጂ ሌሎችም በርካታ የወደፊት እቅዶች አሉት።

ዛሬም እኛ ወጣቶች ይህን የመሰሉ ለብሔራዊ ልማት አጋዥ የሆኑ፣ የወጣቱን ተሳትፎ የሚጠይቁ፣ ድርጅቶች ቢስፋፉና የወጣቱን ችሎታና ፍላጎት ቢያጎለብት ጥሩ ይሆናል ብለን እናስባለን። ቅን ፍላጎቱና መተባበሩ ካለ መንግሥት ይሄን መሰል ድርጅት እስኪያቋቁም ሳንጠብቅ ራሳችን ማቋቋም እንችላለን።

ይህን መሰል ምግባረ ሰናይ ድርጅት ለማቋቋም ባንችል እንኳ፣ አገራችን ብሔራዊ የልማት ጥሪ ስታቀርብልን እያንዳንዳችን በሙሉ ፈቃደኝነት መሳተፍ የውዴታ ግዴታችን እንደሆነ ማመን ያስፈልጋል። ምክንያቱም እኛ ዛሬ እየተጠቀምንባቸው ያሉ የአይን ማረፊያ የሆኑት ቅርሶች በሙሉ ያለፈው ትውልድ የደከመባቸው ናቸው። እስቲ! ራሳችንን ለአገሬ ምን ሰርተናል ብለን እንጠይቅ? ብዙ ነገር ልንፈጥር የምንችል ይመስለኛል። ሌሎች በቅርስነት የተውልንን ነገር በአይናችን እያየን በአድናቆት ከመመልከትና በእነሱም ከመገረም ይልቅ እራሳችን የዚህ ታሪክ ተካፋይ የምንሆንበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅብናል። ሌላው በደከመበት የእጅና የአዕምሮ ውጤት ስንጠቀም ደግሞ ባለዕዳዎች መሆናችን ለሁላችንም ሊታሰበን ይገባል። ይህ ነው የኔ እምነት....

ብዙ ወጣቶች ላገራቸው መልካም ነገር ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ሲያወሩ ይሰማሉ። በአፍ መናገር ብቻውን በራሱ ፍሬ ነገር ሊሆን አይችልም። ወጣቱ በወጣትነቱ ማድረግ የሚገባውን ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል። በኢኮኖሚ አድገዋል የሚባሉ አገሮች እዚያ ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት የወጣቱ ተሳትፎ ታክሎበት ነው። ሁሉም ወጣት የአገሩን ብሔራዊ ጥቅም እንደግል ጥቅም መመልከት አለበት!፡ እንደዚህ ዓይነቱ መልካም ዝንባሌም የወጣት ጡረተኞችን ቁጥር ሊቀንስም ይችላል።

ወጣቱ በቁሳዊ ነገሮች ብቻ ተወጥሮ የሚኖረው እስከመቼ ይሆን? አንዳንድ ጊዜ ለአዕምሮአዊው ስራም ፋታ ሊኖረን ይገባል። በወጣትነታችን የተፈጥሮን ውበት ለአንድ አፍታ ቆመን ለማድነቅ ጊዜ አጥተን "እራሱን ያጣ ትውልድ" የምንባለው እስከመቼ ነው? በዋል ፈሰስ እየሆንን የምንኖረው እስከመቼ ነው? በብሔራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ስንሳተፍ አንድ እራሳችን የምናዝናናበት ነገር እንደፈጠርን ማወቅ አለብን።
አንዳንድ ወጣቶች ሁልጊዜ መንግሥት ለነሱ ማድረግ የሚገባው ነገር እንዳለና ማግኘት የሚገባቸውን ነገር ሲያገኙ ብቻ መኖር እንደሚችሉ የሚሰማቸው አሉ። "አሸናፊ!" የምንለው ወጣት ግን ከማንም ምንም ሳይሻ በሁለት እግሩ መቆም የሚችል ነው። በብሄራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ወጣቱ በፍላጎት መሳተፍ አለበት የምለውም ይህን መሰሉን ድክመታችንን ማስወገድ እንድንችል ነው።

CGRDA

ያለፈው ትውልድ ብዙ መልካም ነገሮችን ሠርቶ አልፏል። እኛም ልክ እንደነሱ እንደየችሎታችንና አቅማችን ሠርተን ብናልፍ መጪው ትውልድ ደግሞ ከኛ የሚማረው ነገር ሊኖር ስለሚችል ራሱን ሊጠይቅ ይችላል። አንድ ወጣት የአቅሙን ያህል ግዴታውን ከተወጣ በመጪው ትውልድ ተጠያቂነት አይኖረውም ማለት ነው።

በእርግጥ አንድ ነገር ሠርቶ ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ቀላል ነገር አይደለም። በጣም ብዙ ድካምና የመንፈስ ጥንካሬን የሚጠይቅ ነው። ይህን መሰሉን መልካም ነገር ለማድረግ አንዳንድ ጊዜ ያለንበት የኑሮ ደረጃ ሊገድበን ይችላል። ነገር ግን እስከዛሬ ድረስ በቅርስነት የታዩት ውድ ቅርሶቻችንን መንከባከብና ተቆርቋሪ መሆን እንዴት ያቅተናል?

የአከሱም ወይም የላሊበላ የመሳሰሉት ቅርሶች ባለቤት መሆናችንን በኩራት ማውራት ብቻውን ተቆርቋሪ አያሰኝም። የእኛን የመንፈስ ጥንካሬ የሚጠይቀው፣ የይድረስልን ጥሪያቸውን ሲያሰሙን እኛም የተግባር ተሳታፊ መሆን ስንችል ነው። እጅግ በጣም የሚገርመው ደግሞ ላገራችን ቅርሶች ተቆርቋሪ ሲሆኑ የሚታዩት የባዕድ አገር ሰዎች መሆናቸው ነው። ተቆርቋሪነቱ እንኳ ቢቀር ያሉንን ቅርሶች ያሉበት ቦታ ድረስ ሄዶ በአይን ማየትና ማድነቅ እንዴት ያቅተናል? በኛ አገር ይህን የመሰለው በጎ ልማድ ቢኖር ወጣቱን ወደ ብሔራዊ ልማት ለመጥራት ብዙ ባልከበደ ነበር።

እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ለወጣቱ ዓይን ማረፊያ የሚሆኑ ሙዚየሞች አሉ። ወጣቱ እነዚህን ነገሮች እየሄደ የመመልከት ልምድ ቢኖረው፣ ለብሔራዊ ልማት ያለው ስሜት ጥሩ ይሆን ነበር። ግን ምን ያደርጋል.... እንኳን በአዘቦቱ በዕለተ እሁድ እንኳ ሄዶ የሚጎበኛቸው ሰው የለም።

ወጣቱ ስለወጣትነቱ ሲያስብ ወጣትነት ምን እንደሆነ ሊያውቅ ይገባል። ተፈጥሮን የሚያደንቅበት ጊዜ ሊኖረው ያስፈልጋል። ሁልጊዜ በዋልፈሰስ መሆን እስከመቼ! አንዳንድ ጊዜም ስለ ሞራል ማሰብ አለብን። አስተሳሰባችንም አለም አቀፍ እንዲሆን መጣር ይገባናል።

አንድ ወጣት ራሱን ለብዙሃን ደስታ ከመሰዋት የበለጠ የሚያሰደስተው ነገር ፈጽሞ የለም። በብሔራዊ ልማት ዘርፍ የመሳተፍ ልማድ እየጎለበተ ሲሄድ አገርን በልማት ከመጥቀም ባሻገር፣ የወጣቱም አመለካከት ይቀየራል። ለወደፊት በአገሪቱ እድገት ላይ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ሙስና፣ ጎታችነት፣ ቢሮክራሲያዊ አሰራርም እየተሻሻሉና እየጠፉ ይሄዳሉ። ምክንያቱም ወጣቱ ከልጅነቱ ጀምሮ አዕምሮውን በመልካም ነገር ገንብቶታል.... ሐላፊነትና ተቆርቋሪነትም ይሰማዋል። የብሔራዊ ልማት እንቅስቃሴ እየጎለበተ ሲመጣ ደግሞ ብሔራዊ ልማት ብሔራዊ ልማድ ይሆናል።

CCRDA

"ለነገው ብሩሕ ቀን"

በዳዊት ንጉሡ
ደረጃ ዘጠነኛ

ለነገው ብሩህ ቀን.... ለነገው ብሩህ ቀን
ለሀገር ግንባታ እንሥራ ተባብረን፡፡

ልጅነት አብቅቷል.... ዛሬ ከፍ ብለናል
ውሃውን ከእሳቱ... መለየት ችለናል
መብታችንም ፀድቆ..... ትኩረት ተሰጥቶናል....

ከእንግዲህ..... ከእንግዲህ.....
ለሀገራችን ዕድገት.... ለሕዝብ ብልጽግና
ወጣቶች በሙሉ... ባንድ እንሁንና!

ለዕድገት አነሳስተን.... ብሩህ አዕምሮአችንን
በየአቅማችን ሠርተን..... በየችሎታችን
ልማቱን አስፋፍተን.... ድህነት እርቆን
ኢትዮጵያችን አድጋ..... መኖር እንሻለን፡፡

ወጣት ሴቶቻችን... በልማት ተሳትፈው
መደፈር መጨቆን.... ሁሉም ቀርቶላቸው፡፡
የጎዳናም ሕይወት.... በትብብር ጠፍቶ
የወጣቶች ጥቅም..... በሁሉም ዘርፍ ጎልቶ.....

ከእንግዲህ..... ከእንግዲህ..... ከእንግዲህ
ኢትዮጵያ እንዳትባል..... ሁልጊዜ ድሃ አገር
ከሥሩ እንዲነቀል.... የዜጎቿም ችግር፡፡
እኛ እንቡጥ ወጣቶች.... በሕብረት እንሥራ
አልበቅል ያለውን.... ፍሬ እንድናፈራ፡፡

ባገራችን መሬት..... ባገራችን ምድር
ሁሉም ደስ እያለው... በልቶ ጠግቦ እንዲያድር፡፡

እኛ ወጣት ዜጎች..... ተባብረን በጋራ
በየተሰጥኦችን.... ከተሠራ ሥራ፡፡

ድንግል መሬታችን..... ጋራው ሸንተረሩ
ተጠርጎና ፀድቶ..... ከሾህ ከቆንጥጣ፡፡

ቡቃያው አብቦ..... ብሩህ ፀሐይ ወጥታ
ምድራችን በአዝርዕት.... አብባና ፈክታ፡፡

ሠላም ባገር ሰፍኖ..... ሥንፍና ተባሮ
መኖር እንችላለን.... እኛም አዲስ ኑሮ፡፡

GCRDA

የወጣቱ ብሩህ ተስፋ



በሰለሞን መላኩ

የኢትዮጵያ ወጣቶች እምቅ ችሎታዎች

በፍፁም ኃይሉ
ደረጃ አሥረኛ

ኢትዮጵያውያን ወጣቶች አብዛኛው ፍላጎታቸውና የማምረት ችሎታቸው ጎልቶ ባይታይም፣ ከብዙ በጥቂቱ በሥራ ላይ የዋሉ እንቅስቃሴዎች እንዳሉ የማይዘነጋ እውነት ነው፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች ወይም በእንግሊዘኛው አጠራር (Interestes) ምን ምን ናቸው? እስከዛሬስ በስራ ላይ እንዴት ውለዋል? ካልዋሉስ ይህን አዲስና ትኩስ ችሎታ አስሮ የያዘው ምን ይሆን? ለነዚህና ለሌሎችም ዐበይት ጉዳዬች ቀጥሎ መልስ ለመስጠት ይሞከራል፡፡

እናት ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀን ከቀን ለጋ ህፃናትን ብታፈራም፣ በሞት የሚለያትም በዚያው መጠን መሆኑን የማይጠረጠር እውነታ ነው፡፡ አሁን አሁን ግን ይህ እውነታ መንገዱን ለቅቆ ሚዛኑ በህፃናቱ ላይ መድፋት ከያዘ አመታት አስቆጥሯል፡፡ ታዲያ! እነዚህ ተወልደው ያደጉ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሲሆኑ፣ በሚፈልጉበትና በሚሹት ሥራ ላይ ተሰማርተው ሙያቸውን ሲያጎለብቱ አይታዩም፡፡ እነዚህን ወጣት ሀይሎች ከበለፀጉት ሀገራት ጋር ስናነፃፅራቸው የሰማይና የምድር ያህል ተራርቀው ይታያሉ፡፡

“የህፃናት አእምሮ እንዳልተፃፈበት እንደ አንድ ንፁህ ነጭ ወረቀት ነው፡፡” የሚል አባባል አለ፡፡ በሀገራችንም በተለያዩ ስፍራዎች ይህንንና የዚህን ዓይነት የሕፃናትን አዕምሮ የሚያጎለብቱ ጥቅሶችን ከተለያዩ ሰዎች እንሰማለን፡፡ በአንፃሩም በአፋቸው ይህን የሚሉ ግለሰቦች በወጣት ታዳጊ የሀገር ተረካቢ ትውልዶች አእምሮ ውስጥ መጥፎና አስጸያፊ የሆኑ ሊታረሙ የማይችሉ ነገሮችን ሲቀርፁባቸው ይስተዋላል፡፡ ይህ መጥፎ ድርጊት በአእምሮአቸው የተቀረፀው ወጣቶች አድገው ሀገርን በማልማት ፋንታ እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ይጎዳሉ፡፡ ለሀገርም ሸክም ይሆናሉ፡፡

ስለዚህ ከላይ እንደተገለፀው ጥቅስ በነዚህ ለጋ ወጣቶች አእምሮ ውስጥ ንፁህ ነገርን ማስቀመጥ የእያንዳንዱ ወላጅ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ አለብን፡፡

ወላጆች ሊያደርጉት የሚገባና የእነዚህን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ፍላጎት ሊረዱ፣ ተረድተውም ሊያበረታቱት የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ አንድ ወጣት የሥዕል፣ የሙዚቃ፣ የድርሰት፣ የድራማ የህክምናና የምህንድስና ወይም የፍልስፍና ሌሎችም ከነዚህ አንዱን ስጦታ ሊኖረው ይችላል፡፡ እነዚህን ችሎታዎቹን የማበረታታት ኃላፊነት የወላጅ ይመስለኛል፡፡ “ፍላጎትህን እቃወማዋለሁ.... ይህን ትተህ ሌላ ምረጥ!” ማለት ያንን ወጣት ወደ ማይፈልገው መስክ መገፋፋት ነው፡፡ የዚያን ወጣት ህይወትም ማጨለም ነው፡፡ እንዲሁም በውስጡ ያለውን ትኩስ ሙያዊ ፍላጎት መግደል መሆኑን መገንዘብ ይገባናል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የዚህን ትኩስ ዜጋ ፍላጎት ከመግታት ይልቅ፣ ለታዳጊ ወጣቱ ሊደረግ የሚገባውን በማድረግ አዳዲስ መፍትሔዎችን ብንፈልግ ወጣቱን፣ ቤተሰቡን፣ አካባቢውን ብሎም ሀገሩን የሚያበለፅግ መፍትሔ አገኘን ማለት ነው፡፡

በዘመናችን ያሉትን አንቱ የተባሉትን ታላላቅ ሰዎች ለምሳሌነት መውሰድ እንችላለን፡፡ እነዚህ ሰዎች ሲወለዱ አብሮአቸው ከተወለደው ጽኑ ፍላጎትና አስተሳሰብ ጋር አብረው አድገው ከዕለት ዕለት ህይወታቸው ጋር ተያይዞ አሁን ካሉበት ደረጃ ላይ የደረሱት ከወላጆቻቸው በተሰጣቸው በጎ ድጋፍና

CCRDA

ምክር የተነሳ ነው፡፡ የወላጆቻቸው ተፅእኖ እያለባቸው ለእንደዚህ ዓይነቱ በጎ ሥራ የደረሱም ብዙዎች ናቸው፡፡ ለአርአያነት የአለማችንን ዕውቁን አሜሪካዊ ሙዚቀኛ ማይክል ጃክሰንን ብንወስድ፣ በህፃንነቱ የተጠናወተውን የሙዚቃ ፍቅር ለመወጣት ሲል ከባቢ ቤት እየተደበቀ ጊታርና ሌሎች የሙዚቃ መሳሪያዎችን ይጫወት እንደነበር የልጅነት ታሪኩ ይናገራል፡፡ ማይክል ይህንን ያደርግ የነበረው አባቱ እንደነፍሱ የሚወደውን ሙዚቃ ስለሚነቅፍበትና ይህንን እንዳያደርግ ዘወትር ስለሚከለክለው ነበር፡፡ ታዲያ የሚገርመው ነገር ማይክል ይህንን ሲያደርግ ገና የ4ዓመት ሕፃን እያለ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ታላቅ ሰው በልጅነቱ ይህን ያህል ጫና እያለበት የተከበረ ሙያውን ሳያስደፍር በማቆየት ዛሬ በእጅጉ የገነነ የዘመናችን የሙዚቃ ቁንጮ ለመሆን በቅቷል፡፡ ታዲያ! ይህንን የማይክል ታሪክ ስንመለከት ያለንበት ህብረተሰብ ያሰፈረው ክፋ ባህልና ወግ መነሳት እንደለበት እናምናለን፡፡ ልጆችን ያለ ውዴታቸውና ያለ ፍላጎታቸው፣ አቅማቸውና ሙያቸው ከሚፈቅድላቸው መጠን በላይ ማሰራትና ወጣቶችን ወደማይፈልጉበት ሙያ መገፋፋት ወይም ደግሞ የሚፈልጉትን ሙያ መከልከል ከንቱ መሆኑን መገንዘብ አለብን፡፡ ልጆችን ብዙ ብናበረታታና ከሚማሩት የቀለም ትምህርት ጎን ለጎን ፍላጎታቸውን የሚገልፁበትን ብናስጠናቸው እጅግ አስደሳች ውጤት እንደሚሰጠን መገመት የሚያዳግተን አይመስለኝም፡፡ እናንተስ! ወጣቶች በዚህ በልጅነት ህይወታችሁ ስንቱን ለመሰራት አቅዳችኋል? ባላችሁስ ትኩስ አእምሮ ምን ያህል ለመስራት አልማችኋል? ግባችሁን እስክትመቱ ድረስ መትጋትን አትርሱ፡፡

CCRDA

ወጣቱ

በተስፈኛው
ደረጃ አሥረኛ

ሥራ አጥነት ነግሶበት
የኑሮ ድርና ማግ ጠፍቶበት፡፡

ተብሎ ወጣት ጡረተኛ
በአላፊ አግዳሚ መንገደኛ፡፡

ይኖረዋል "ኖረ" ከተባለ
በዋል ፈሰስ እየማለለ፡፡

ግና! ግና
ይታየኛል ብሩህ ደመና
በወጣቱ ንቃተ ህሊና፡፡

እናም..... እናም.....
በሰናይ ባህርይው ታንጸ
ማህበራዊ እሴቶች ተላብሰ፡፡

ከሱስ ባርነት ተላቆ
ከእኩይ ምግባር ርቆ፡፡

ለመሆን ባለ አእምሮ
በዓላማ ተምሮ
በራስ አገዝ ማህበራት ተዋቅሮ፡፡
በመሠረተ ልማት ተሳትፎ
ችግሩን ይጥልና ቀርፎ

ቅጽል ስሙን ይሻርና
ደግሞ ተወልዶ ያድርና!

ስሙን አድሶ
ይባላል ወጣቱ
የሆነ ብርቱ
የአእምሮ ባለሀብቱ
ብሩህ ተስፋ ለሀገሪቱ
የታደሰ ማንነቱ
ጥሪት የሀገሪቱ፡፡

CCRDA

የወጣቶች አንድነት



በወርቅነህ በዙ

የዳኝነት ሥራ

1.1 የዳኞች ስም

1.1.1 የልብ ወለድና የሥነ ግጥም ዳኞች

ደራሲ ሲሳይ ንጉሡ ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ሰብሳቢ
ደራሲ ማሞ ውድነህ ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር አባል

1.1.2 የፖስተር ስዕሎች ዳኞች

ሰዓሊ ኃይሉ ፀጋዬ የስዕል ት/ቤት መምህር ሰብሳቢ
ሰዓሊ ተስፋዬ ወ/ስላሴ የስዕል ት/ቤት መምህር አባል

1.2 ለውድድር የቀረቡ ሥራዎች

1.2.1	አጭር ልብ ወለዶች	83
1.2.2	ሥነ ግጥሞች	100
1.2.3	የፖስተር ስዕሎች	110

1.3 የግምገማ ሥራዎች

1.3.1 ለልብ ወለዶችና ለሥነ ግጥሞች

አንደኛ ደረጃ- ለውድድር የቀረቡት ባሉበት ሁኔታ ማጣራት
ሁለተኛ ደረጃ- ከልብ ወለዶች ከግጥሞች መካከል ከእያንዳንዳቸው ሃያ ሥራዎችን መምረጥ
ሶስተኛ ደረጃ- ከተመረጡት የፈጠራ ሥራዎች ውስጥ ሶስት መርጠ ማውጣት
አራተኛ ደረጃ- ደረጃቸውን መወሰን

1.3.2 የፖስተር ስዕሎች

የመመዘኛ ነጥቦችን የሚያሟሉ የፖስተር ስዕሎችን መለየት... በዚህም መሠረት ከቀረቡት 110 የፖስተር ስዕሎች መካከል 16 ፖስተሮች የሌሎች ቅጂ በመሆናቸው ሶስት ፖስተሮች ከተጠየቀው መጠን በላይ ስለሆኑ፣ 63 ፖስተሮች የቴክኒክ ጉድለት ስለነበራቸው ከውድድር ውጭ ሆነዋል።

1.4 የመመዘኛ ነጥቦች

CCRDA

1.4.1 የአጭር ልብ ወለድ

ይዘት- እምቅ ችሎታ ሚና ፈጠራ እና የወጣቱ ሕይወት
ቅርጽ- የቃላት ቁጥብነት... ግልጽ አረፍተነገሮች... የአንቀጾች አገነባብ.... አንፀባራቂነትና ሕይወት ያላቸው አገላለጾች... የጥቅሶችና የምሳሌዎች አገባብነት.... ወጥነት ተቀባይነት ሥርዓተ ነጥብ...

1.4.2 የሥነ ግጥም

ይዘት- እምቅ ችሎታ.... ፈጠራ እና የወጣቱ ሕይወት
ቅርጽ- ቤት አመታት.... ድምፅ.... ግልጽነት.... ወጥነት... የግጥም ኃይል...

1.4.3 የፖስተር ስዕሎች የመመዘኛ ነጥቦች

- የተመልካችን ዓይን የሚማርክ...
- መልዕክቱን ለተመልካች በግልጽ የሚያስተላልፍ....
- ለመገናኛ ብዙሀን ጠቀሜታ የሚውል....
- ኪነጥበባዊ ውበቶችን ተምሳሌዎችን ያካተተ....
- ቀለማቸው የሰው ዓይን የሚስብ....
- የሃሳብና የቴክኒክ ወጥነት ያላቸው.....
- ቀላልና ግልጽ የሆኑ....
- ለሕትመት የማያስቸግሩ....

1.5 የነጥብ አሰጣጥ

1.5.1 ለይዘት - 50%
1.5.2 ለቅርጽ - 50%

1.6 የውድድር ውጤቶች

1.6.1 በአጭር ልብ ወለድ ከ1-3ኛ

- ዘሪሁን ወርቅነህ
- ማንደፍሮ ንጉሴ
- ምህረት ተስፋዬ


1.6.2 በፖስተር ስዕል

- ብሩክ ማሞ
- ገዛኸኝ ኡርጋ
- ሮማ ታደሰ

CCRDA

CHRISTIAN AID & ITS ETH. NGO PARTNERS (CAPNET)

የክርስቲያን ኤይድና መንግስታዊ ያልሆኑ ተባባሪ ድርጅቶች



CRDA

CHRISTIAN AID
MAY, 1998
ADDIS ABABA, ETHIOPIA

Published by Roots Africa
Tel. 52 16 20
Addis Ababa ~ Ethiopia.